ሰዎችን እንዲያጠራጥር ምን ማድረግ እንዳለብን ያስተምረናል።

*16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ገንዘብን በተመለከተ ሰይጣን እንዴት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እንዳሸነፈ ግለጽ። ለ) ከላይ የተጠቀሰው ምክር መሪ ያለውን ቅንነት እንዲጠብቅና በኃጢአት እንዳይወድቅ እንዴት እንደሚረዳው ግለጽ?*

## 8. እስከ መጨረሻው ያለ መጽናት ኃጢአት

*17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉና በጥሩ ሁኔታ መምራት የጀመሩ በስተመጨረሻ ግን በተለያየ ምክንያት አመራራቸው የተበላሸባቸውን ሰዎች ስም ዘርዝር። ለ) መንፈሳዊ ዝናቸውን ያበላሹባቸውን ኃጢአቶቻቸውን ዘርዝር። ሐ) በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት የጀመሩ፣ ሆኖም አጨራረሳቸው ያላማረ የቤተ ክርስቲያንን መሪዎች የምታውቅ ከሆነ፣ አጨራረሳቸው ሊያምር ያልቻለባቸውን መንገዶች አብራራ። መ) እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ በመልካም መሪነት ያለንን ዝና መጠበቅ አስቸጋሪ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?*

በሕይወት ውስጥ ካሉ አሳዛኝ ነገሮች አንዱ እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል የተጠቀመባቸው ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሕይወታቸው መጨረሻ ላይ በኃጢአት ሲወድቁ ነው። በዘመናችን መላው ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር በታማኝነት መኖር የሚችሉት ጥቂቶቹ ብቻ ነው የሚመስሉት። በጥሩ ሁኔታ ይጀምራሉ። ለብዙ ዓመታት ያገለግላሉ። ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች፣ እያረጁና ስኬታማ እየሆኑ ሲመጡ፣ በኃጢአት ይወድቃሉ። በጥሩ ሁኔታ የሚጀምሩ ብቻ ሳይሆን፣ በጥሩ ሁኔታ የሚፈጽሙት ይባረኩ! በተለይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሕይወታቸው ሁሉ በታማኝነት እግዚአብሔርን የማገልገል ችግር አለባቸው።

የዕብራውያን መጽሐፍ የተጻፈው ለረጅም ዓመታት በታማኝነት ኢየሱስን ላገለገሉ ሰዎች ነው። ነገር ግን የአይሁዳውያን ማሳደድ እየበዛ ሲሄድ፣ ወደ ቀድሞው የብሉይ ኪዳን እምነታቸው



ለመመለስ የተፈተኑ ናቸው። ለአማኞቹ ያ እግዚአብሔርን ለመከተል ተቀባይነት የሌለው መንገድ እንደ ሆነ ከተናገረ በኋላ፣ ጸሐፊው መንፈሳዊ ሩጫቸውን «በትዕግሥት» እንዲፈጽሙ ይነግራቸዋል (ዕብ. 12:1)። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ስኬት በክርስትና እርምጃችን ወይም በአመራራችን አሁን በጥሩ ሁኔታ መሥራታችን አይደለም። ሕይወታችንን በጥሩ ሁኔታ መፈጸም ነው።

በመሪዎች ፊት ከተጋሰጡ ትልልቅ አደጋዎች መካከል በዓለም መስፈርት መሠረት የሚለካ ስኬት አንዱ ነው። ያ ስኬት ምናልባትም ዓለማዊ ሥራችን በሚያስገኝልን በገንዘብ ሊሆን ይችላል። ወይም ምናልባትም ጥሩ ወንጌላዊ በመሆን መልካም ዝና ማግኘት ወይም ጥሩ ሰባኪና ተናጋሪ በመሆን ታዋቂነትን ማግኘት ሊሆን ይችላል። እኛ ዝነኛ ስንሆንና ብዙ ቁሳዊ በረከቶችን ስናገኝ፣ ያ በሕይወታችን በጣም አደገኛው ጊዜ ነው። ያን ጊዜ ነው አብዛኛዎቹ መሪዎች የሚወድቁት። ነገሮች ሁሉ መልካም ሲሆኑና እግዚአብሔር ሲጠቀምብን ነው በኃጢአት የመውደቅ አደጋ ውስጥ የምንገባው።

መጽሐፍ ቅዱስን፣ በተለይም በይሁዳ ላይ ስለ ገዙ ነገሥታት፣ ስናነብብ፣ አብዛኛዎቹ መልካም ዝና የነበራቸው መንፈሳዊ ነገሥታት ስኬታማ በሆኑበት ጊዜ በኃጢአት እንደ ወደቁ እናነብባለን። እስቲ አንዳንዶቹን እንዘርዝር፡-

ሀ. ንጉሥ ሳኦል፡- እግዚአብሔር አሞናውያንን ለማሸነፍ ተጠቅሞበታል (1ኛ ሳሙኤል 11)። በጣም ስኬታማ የሆነና በሕዝቡ ዘንድ ታላቅ የጦር መሪ በመሆኑ የተከበረ ነበረ። ነገር ግን እግዚአብሔርን በከፊል ብቻ ይታዘዝ ስለነበረ እግዚአብሔር ናቀው። እግዚአብሔር ታላቅ መሪ እንዲሆን ለመረጠው ሰው እንዴት ያለ አሳዛኝ አጨራረስ ነው። በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔርን ምሪት ከመፈለግ ይልቅ ወደ ጠንቋይ ቤት እንደ ሄደና በጦር ሜዳም ራሱን እንደ ገደለ እንመለከታለን (1ኛ ሳሙ. 31)።

ለ. ንጉሥ ዳዊት፡- ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ፣ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ታላቅ ዘማሪ የሆነ፣ የእስራኤልን ግዛት እጅግ ያስፋፋ ለእግዚአብሔርም ሕዝብ ታላቅ ዘመን ያመጣ ሰው ነበረ። እርሱ ስኬታማ ከሆነ በኋላ ነው በዝሙት የወደቀውና ከታላላቅ ተዋጊዎቹ አንዱን የገደለው (2ኛ ሳሙ. 7:1፤ 8:11)። እርዮን በዳዊት ዘመን ከነበሩ 30 ታላላቅ ተዋጊዎች መካከል አንዱ ነበር (2ኛ ሳሙ. 23:39)። እርሱ ስኬታማ ከሆነ በኋላ ነበር ባለው ወታደራዊ አቅም ተኩራርቶ ወታደሮቹን ያስቆጠረው።

ሐ. ንጉሥ ሰሎሞን ንግሥናውን የጀመረው ሕዝቡን የሚመራበትን ጥበብ እንዲሰጠው እግዚአብሔርን በመጠየቅ ነበር። በራሱ ጥበብ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት እንደማይችል ያውቃል። ዳዊት የጀመረውን ድንበር የማስፋት ሥራ ቀጥሏል። ለእግዚአብሔር ታላቅ መቅደስ፣ አስገራሚ ቤተ መንግሥትና ሌሎችንም ነገሮች አሠርቷል። ነገር ግን ተጽዕኖውን በመላው ዓለም ለማስፋት ከመፈለጉ የተነሣና ከፍትወት የሚገኘውን ደስታ በመውደዱ ወደ ጣዖት አምልኮ የመሩትን በርካታ ሴቶችን አግብቷል (1ኛ ነገ. 11:1-6)። በሽምግልናው በጻፈው መጽሐፈ መክብብ ላይ፣ ሰሎሞን የዓለምን ደስታ ሲፈልግ ዘመኑን እንዳቃጠለ ጽፏል። በመጨረሻም የእርሱ ኃጢአት የእግዚአብሔር ሕዝብ በመከፋፈሉ ለሜናዊ መንግሥትና ደቡባዊ መንግሥት ሆነች።

መ. ንጉሥ ዓሣ፡- እግዚአብሔር ጠላትን ለማሸነፍና በይሁዳ መንግሥት ላይ መንፈሳዊ ተሐድሶ ለማምጣት ተጠቅሞበታል። ነገር ግን ሲያረጅ፣ የገሠጸውን ነቢይ አሰረ፣ ሕዝቡንም መጨቆን ጀምሮ ነበር (2ኛ ዜና 14-16)።

ሠ. ንጉሥ ኢዮሳፍጥ፡- ጠላት ሊያሸንፈው ሲል፣ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ በእግዚአብሔር በመታመኑ ጠላት ሲሸነፍ ተመልክቷል። በይሁዳም ታላቅ መንፈሳዊ ተሐድሶ አምጥቷል። ነገር ግን ለፖለቲካ ወዳጅነት ሲል፣ ለልጁ እግዚአብሔርን ከማያምነው



የእስራኤል ንጉሥ ልጅ የሆነችና በኣልን የምታመልክ ሚስት ሰጠው። ይህች ሴት የበኣልን አምልኮ ለይሁዳ አስተዋውቃለች፣ በመጨረሻም በምድሪቱ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ሊመጣ ችሏል። ለልጁ ያመጣለት ሚስት ከአንድ ልጅ በስተቀር የኢዮሳፍጥን ዘር በሙሉ ገድላለች። ሰይጣን ይህንን ሁኔታ ተጠቅሞ የመሢሑን መምጫ የዘር ሐረግ ለማጥፋት ተዳርሶ ነበር (2ኛ ዜና 18-20)።

ረ. ንጉሥ ኦዚያን፡- የይሁዳ ምድር ካየቻቸው ታላላቅ የጦር መሪዎች አንዱ በመሆን ይታወቃል። የይሁዳን ምድር በዳዊትና በሰሎሞን ጊዜ እንደ ነበረው አስፋፍቷል። ነገር ግን ትዕቢት ይሰማውና መሪ በመሆኑ ያሰኘውን ማድረግ እንደሚችል አሰበ። የእግዚአብሔርን ቃል በመጻረር፣ ወደ መቅደሱ በመሄድ ለእግዚአብሔር ለማጠን ሞከረ። ይህ አገልግሎት የተፈቀደው ለካህናት ብቻ ነበር። እግዚአብሔርም በለምጽ መታው፣ በተቀረው የሕይወት ዘመኑ ሁሉ ከሕዝቡ ተለይቶ መኖር ነበረበት፣ ልጁም በእርሱ ቦታ ሆኖ መምራት ጀመረ (2ኛ ዜና 26)።

እነዚህ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በቅድስና ስላልዳኑ ታላላቅ የእግዚአብሔር መሪዎች የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው። ሁሉም በጥሩ ሁኔታ የጀመሩና እግዚአብሔርን የሚወድዱ ነበሩ። እግዚአብሔርም በታላቅ ኃይል ተጠቅሞባቸዋል። ነገር ግን በኃጢአት ወደቁ፣ አብዛኛውን ጊዜ ኃጢአታቸው ኩራትና ከዓለም ጋር ማመቻመች ነበር። ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላትና ጥፋትን ለማምጣት የሰይጣን መሣሪያ ሆኑ። ታላላቅ የሆኑ መሪዎች በዚህ መንገድ ከወደቁ፣ እኛም በተመሳሳይ በኃጢአት ልንወድቅ እንደምንችልና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመጉዳት የሰይጣን መሣሪያ ልንሆን እንደምንችል እያስጠነቀቀን? በዘመናችን ቤተ ክርስቲያን በርካታ እግዚአብሔር በአንድ ወቅት በታላቅ ኃይል የተጠቀመባቸው ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን የሚያመጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ

20:29-31 ላይ እንዳስጠነቀቀው የሐሰት ትምህርትን የሚያመጡ ናቸው። እንዳለመታደል ሆኖ፣ በደርግ ዘመን እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል የተጠቀመባቸው ነገር ግን ታዋቂ ሊቦች የሆኑና ቤተ ክርስቲያንን የዘረፉ ሰዎች አሉ። ሌሎች ኢየሱስን እንዲከተሉና መንግሥቱን እንዲያዩ ከማመልከት ይልቅ በምድር ላይ የራሳቸውን መንግሥት የመሠረቱ ናቸው።

የምንኖረው በእግዚአብሔር ላይ መጽናት አስቸጋሪ በሆነበት ዘመን ነው። አስቸጋሪ የሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው። <u>አንደኛ</u>፣ የምንኖረው በታላቅ የበረከት ዘመን በመሆኑ ነው። ነገሮች አስቸጋሪ ከሆኑበት ዘመን ይልቅ ነገሮች ሁሉ መልካም በሆኑበት ዘመን ለእግዚአብሔር መታመን ያስቸግራል። ከደርግ ዘመን ይልቅ አሁን ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን አስቸጋሪ ነው። በደርግ ዘመን ለሕይወታችን በእግዚአብሔር ላይ እንታመን ነበር። ነገር ግን አሁን ነጻነትና ቁሳዊ በረከቶች በበዙበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ላይ መደገፋችንን አቁመን እግዚአብሔር በሰጠን ቁሳዊ በረከቶች እንዴት እንደምንደሰት ነው የምናስበው። እንዳለመታደል ሆኖ በበረከት ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ ልብ ይቀዘቅዛል። የበለጠ ቁሳዊ በረከቶች እንዲመጡላቸው ለማድረግ ሁኔታዎችን ማምታታት ይጀምራሉ። ከዚያ የተነሣ በርካታ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን ተከራርተዋል። «ሃብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም እንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለሆንክ፣ ጐስቋላና ምስኪንም ድሃም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፣. . .» (ራእይ 3:17)። ኢየሱስ ቁሳዊ ነገሮች ላይ ከማተኮር ይልቅ የእርሱን ጽድቅና መንግሥት እንድንፈልግ አስጠንቅቆናል (ማቴ. 6:33)።

<u>ሁለተኛ</u>፣ የምንኖረው የክፋት ሥራ እያደገ ባለበት ዘመን ነው። ለአጭር ጊዜ ችግርን መቋቋም ቀላል ነው። ነገር ግን ዕለት በዕለት የሚያጋጥመንንና እያደገ የሚሄድን ችግር መቋቋም ከባድ ነው። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፣ ቻይናውያን እስረኞችን



ማሠቃየት ሲፈልጉ፣ ሰውየውን አስተኝተው በሰውየው ግንባር ላይ የውኃ ጠብታዎችን ይለቁበታል። ሲጀመር፣ ሥቃይ የለውም፣ ስለዚህ እስረኛው «ይህንን እንኳን መቋቋም አችላለሁ» ብሎ ያስባል። ነገር ግን ለብዙ ቀናት በግንባሩ ላይ ውኃ ሲንጠባጠብ ትንሿ የውኃ ጠብታ እጅግ የሚብስ ሥቃይ እየጨመረች ስለምትሄድ ሰውየው ምሕረት እንዲደረግለት መጮህ ይጀምራል። የዘመናችን የክፋት አሠራርም ይህንን ይመስላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዕለት በዕለት እየጨመረ የሚሄድና መሪዎቻችንን ለመቋቋም ችግር እስኪ አስብ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለተኛና ሦስተኛ ትውልዶች ሲገቡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግብዝነትና መንፈሳዊ ለብታ ተስፋፍቷል። በወጣቶች ዘንድ በርካታ ሚዛናዊ ያልሆኑና የሐሰት ትምህርቶች ይታያሉ። የዓለም አመራር ምን እንደሚመስል ብቻ የሚያውቁ በርካታ መሪዎች በብዙ ቤተ ክርስቲያናት የአመራር ቦታ ላይ ተቀምጠዋል። እንደዚያ ያሉ መሪዎች ለእውነት ከመቆም ይልቅ ለሰላም ሲሉ የሚያመቻምቹ ናቸው። ኀሰኝነት ያጠቃው ምድራችንን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያናችንንም ጭምር ነው። በተጨማሪም በርካታ አዳዲስና ግራ የሚያጋቡና የጠለቀ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የሚጠይቁ ትምህርቶች አሉ በኤድስ፣ በውርጃ፣ የሴቶች ሚና በቤተ ክርስቲያንና በማኅበረሰብ ውስጥ ላይ ምን መሆን እንዳለበት በሥነ ምግባር መውረድ ላይ፣ ወጣቱ የምዕራባውያን ባህልን በመቀበሉ በመምጣት ላይ ባለው ፈጣን የባህል ለውጥ ላይ፣ በእስልምናና በሌሎች ኃይልን የሚጠቀሙ ሃይማኖቶች ማደግ ላይና፣ የመሳሰሉት። እነዚህ ሁሉ መንፈሳዊ በሆነ መሪ ላይ ናዳቸውን የሚያወርዱና የሌሎችን ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል መሪው እንዲያመቻምች የሚያደርጉ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ነገሮች መንፈሳዊ በሆነ መሪ በኩል ታላቅ ጽናት የሚጠይቁ ናቸው። መንፈሳዊነታችን እየወረደ እንዳይሄድ በየዕለቱ ራሳችንን ልንመረምር ይገባል። በባህላችን ታዋቂ ከሆነው አሠራር

ይልቅ በእግዚአብሔር ቃል ለመኖር ራሳችንን ልንሰጥ ይገባናል። ብዙ ጊዜ ይህ ማለት አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያደርጉትና የሚያስተምሩትም እንኳ ቢሆን፣ መሪው ብቻውን መቆም አለበት ማለት ነው። ክርስትና የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ አልቆ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ሲወጡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት ነው የሚመስለው። በጣም አሰቸጋሪ ነው። በታማኝነት መጽናት ማለት መንፈሳዊ መሪ የቤተ ክርስቲያንን አካሄድ በመቃወም፣ በእምነቱ የሚጸናና እግዚአብሔር ብቻ እንዲፈርድ የሚፈቅድ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ የሚፈራው አንድ ነገር አለ። መከራን አይፈራም፣ ሞትን አይፈራም። እርሱ የሚፈራው በኃጢአት መውደቅንና በእግዚአብሔር ፊት መውደቅን ነው። ስለዚህ ጳውሎስ በሕይወቱ ሁሉ በየዕለቱ ሕይወቱን እየመረመረ ጠላቱን እንደሚጉስም በክሰኛ የራሱን ገላ እየጐሸመ ለእግዚአብሔር ይገዛል (1ኛ ቆሮ. 9:24-27)። በሕይወቱ መጨረሻ ላይ ጳውሎስ ሩጫውን እንደ ጨረሰና አገልግሎቱን እንደ ፈጸመ ተናግሯል። አገልግሎቱን ፈጽሞ በራስ መተማመን እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ሽልማት መጠበቅ ጀምሮ ነበር(2ኛ ጢሞ. 4:6-8)። ሁላችንም በሕይወታችን መጨረሻ ላይ እንዲህ ለማለት ያብቃን!

> 18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር በሕይወትህ ሁሉ ታማኝ እንድትሆን እንዲረዳህ ጊዜ ወስደህ ጸልይ። ለ) ሕይወትህን መርምር። በሕይወትህ ውስጥ ለእግዚአብሔር ያለህን አገልግሎት ሊያሰናክሉ የሚችሉ ነገር ግን ከዓለም ጋር ማመቻመች የጀመርክባቸው ክፍሎች አሉ? ካሉ፣ እነዚያን ኃጢአቶች አሁኑኑ ተናዘዝ። ሐ) ልክ እንደ ጳውሎስ ሕይወትህን በራስ መተማመንና ምንም የሚቆጭህ ነገር እንዳይኖርና አካልህን የራስህ ባሪያ ለማድረግ «ራስህን የምትጐስምባቸውን» መንገዶች ግለጥ።
>
> 19ኛ ጥያቄ፡- መሪዎች በልባቸውና በአመለካከታቸው የሚፈጽሟቸውን ኃጢአቶች ቃኝ። ሀ) የትኞዎቹ ኃጢአቶች ቤተ ክርስቲያናችሁ ይበልጥ እንድትጐዳ አድርገዋል? ለ) ለየትኞዎቹ ኃጢአቶች ይበልጥ ተጋልጠሃል? ሐ) ከእነዚህ ኃጢአቶች በአንዱ ከወደቅህ፣ በእግዚአብሔር ፊት ለመናዘዝ ጊዜ ውሰድ።



## ሦስተኛ ቀን፡- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በይበልጥ የሚጋለጡባቸው ኃጢአቶች (ክፍል 4)

### መሪዎች ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚሠሯቸው ኃጢአቶች (ክፍል 1)

መሪነት በቀዳሚነት ከሌሎች ሰዎች ጋር አብሮ መሥራትን ያካትታል። ከእኛ ጋር ሽማግሌ ከሆኑ ሌሎች ሰዎች ጋር አብረን እንሠራለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያድጉና እንዲያገለግሉ ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር እንሠራለን። የአዲስ ትውልድ መሪዎች እንዲያድጉና በሽምግልና አገልግሎት እንዲተኩን ልናሳድጋቸው ይገባል። ከሰዎች ጋር ስለምንሠራ፣ ሰይጣን መሪው ከሌሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት ጋ፣ ያለውን ግንኙነት ለማበላሸት ይጥራል። የሚከተሉት ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ያለውን የእግዚአብሔር ሥራ ለማበላሸት ሰዎች እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው አንዳንድ ኃጢአቶች ናቸው።

1. ቅናት፡- እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎችን እንደ ፈለገ እንዳይጠቀም የመቋቋም ኃጢአት ነው።

ዘሪሁን ባለበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ነው። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ለረጅም ዓመታት በታማኝነት ያገለገለ ሲሆን፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥም የተከበረ ነው። በዚያች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም ስጦታ ያለው እስክንድር የሚባል ወጣት አለ። ከዘሪሁን ይልቅ የተማረ ነበር። እርሱ በሚሰብክበት ወቅት፣ ሽማግሌዎች ሳይቀሩ በጣም ነው የሚገረሙት። ይህ ወጣት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ካሉ አንዳንድ ሽማግሌዎች በላይ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት፣ «እስክንድር መጋቢያችን እንዲሆን እንፈልጋለን። መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስገቡትና ሲመረቅ ይመራናል» ብለው ጠየቁ። የእስክንድር ዝና በጨመረ ቁጥር፣

ዘሪሁን መቅናት ጀመረ። «እኔ ለብዙ ዓመታት በዚህች ቤተ ክርስቲያን አገልግያለሁ፣ ነገር ግን እኔን ፈጽሞ እንዲህ ተመልክተውኝ አያውቁም። አንድ ጊዜ እንኳን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንድገባ አልጠየቁም» ብሎ ያስባል። ስለዚህ ዘሪሁን ስለ እስክንድር የሐሰት ወሬ ማስወራት ጀመረ። ከዚያም ፕሮግራሙን የሚያዘጋጁት ሰዎች ለእስክንድር የአገልግሎት ዕድል እንዳይሰጡት ነገራቸው። ከትንሽ ቆይታ በኋላ እስክንድር ተስፋ ቆረጠ። ቤተ ክርስቲያኒቱን ለቅቆ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ገባ፣ በዚያም እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል ተጠቀመበት።

> 20ኛ ጥያቄ፦ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ የተቀቡ ሰዎች ላይ ሲቀኑ እንዴት እንዳየህ ግለጽ። ለ) ዘኁል. 12፡1-5፣ እና 16ን አንብብ። 1) ለምን ይመስልሃል ማርያም፣ አሮንና የቆሬ ልጆች በሙሴ ላይ የተናገሩት? 2) ስለ ኃጢአታቸው የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር? እግዚአብሔር እኛ እያለን ሌላ ሰውን ሲመርጥ ብንቀና እርሱ በምን መልክ ያንን እንደሚመለከተው እንማራለን? ሐ) 1ኛ ሳሙ. 18ን አንብብ። 1) ሳኦል በዳዊት ላይ የቀናባቸውን ልዩ ልዩ ምክንያቶች ዘርዝር። 2) ሳኦል በመቅናቱ ምን አደረገ? መ) በዘመናችን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቀናተኛ የሚሆኑበትን ምክንያት ዘርዝር። ሠ) ከቅናት የተነሣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እርስ በርሳቸው ምንድን ነው የሚደራረጉት? ረ) ይህ ኃጢአት እንዴት ነው እነርሱንና ቤተ ክርስቲያንን የሚጐዳው?

በብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና በብዙ ቤተ ክርስቲያናት በሚገኙ ቡድኖች መካከል አለመግባባት ያለ ይመስላል። ምንም እንኳን በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ የአብዛኛ ዎቹ አለመግባባቶች መሠረት የቅናት ኃጢአት ነው። አንድ ሰው የበላይ ሽማግሌ ሆኖ ሲመረጥ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይቀኑበታል። ከሌላ ቤተሰብ የመጣ ሰው ወይም ከሌላ ብሔር ለመጣ ሰው ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው ወይም ከራሳቸው ብሔር ለወጣ ሰው የሚፈልጉት ሥልጣን ወይም እውቅና ሲያገኝ ይቀናሉ። ወይም አንዳንድ መሪዎች ደግሞ ሌላ ሰው ከእነርሱ በላይ ዝነኛ ሲሆን ወይም ከእነርሱ በላይ ሲቀባ ይቀናሉ።



በብሉይ ኪዳን ውስጥ ቅናት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ትልልቅ ችግሮችን ያስከተለባቸው ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ምንም እንኳን ማርያምና አሮን ሙሴ ያገባትን ሚስት ለምክንያትነት ቢጠቀሙም፣ በዋነኝነት የተቆጡበት ምክንያት ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው የተለየ ግንኙነትና በእስራኤላውያን ላይ ያለው የመሪነት ሥልጣን ነበር። «እግዚአብሔር በአንተ ብቻ ነው የሚናገረው? በእኛስ ውስጥ አይናገርምን?» ብለው አጉረመረሙ። ብዙም ሳይቆዩ፣ ሙሴና አሮን ከመጡበት ጎሣ የሆኑ ሌዋውያን የቆሬ ልጆች፣ በሙሴና በተለይም በአሮን ላይ አጉረመረሙ። ክህነቱ (የእስራኤላውያንን አምልኮ መምራት) ለሁላቸውም ሳይሆን ለአሮንና ለልጆቹ መሰጠቱን አልወደዱትም። እግዚአብሔር በማኅበረሰብ ውስጥ ለሌዋውያ የተወሰነ መንፈሳዊ መሪነትን ሰጥቷቸዋል፣ ነገር ግን ከፍተኛ የሆነውን የመሪነት ደረጃ ለአሮን ቤተሰቦች ነበር የሰጠው። የቆሬ ልጆች አሮንን ከሊቀ ካህንነቱ ሊያወርዱት ሞከሩ።

በሁለቱም ሁኔታዎች የእግዚአብሔር ምላሽ በጣም የከፋ ነበር። ማርያም ወዲያውኑ በለምጽ ተመታች። ምናልባትም ሙሴ ባይጸልይለት ኖሮ ልትሞት ትችል ነበር። (ማርያም ከሁሉም በላይ በመቀጣቷ ምናልባትም ዋነኛዋ አጉረምራሚ እርሷ ሳትሆን አትቀርም።) የቆሬ ልጆችና 250 የኅበረተሰቡ መሪዎች ወዲያውኑ ተገደሉ። በኋላም እስራኤላውያን ለቆሬ ልጆችና ለማኅበረሰቡ መሪዎች መሞት በሙሴና በአሮን ላይ ሲያጉረመርሙ፣ ሌሎች 14,700 ሰዎች ሞቱ። በግልጽ እንደምንመለከተው፣ እግዚአብሔር በመሪነት በተቀመጡ ሰዎች ላይ በቅናት ስንነሣ ደስ አይሰኝም።

የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ንጉሥ ሳኦል፣ ዳዊት በሕዝቡ ዘንድ ባገኘው ዝናና በወታደራዊ መሪነቱ ባገኘው ስኬት ቀና። ዳዊት ጎልያድን ከገደለበት ዕለት እንሥቶ ንጉሥ ሳኦል እስከሞተበት ዕለት ድረስ፣ ቅናት ሲያቃጥለው ነበር። ንጉሥ ሳኦል በዋነኝነት የሚያላስበው እንዴት ዳዊትን እንደሚገድል ስለነበረ፣

ሕዝቡን ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊመራ አልቻለም። ሳኦል ሲበዛ በቅናት ክመያዙ የተነሣ በሕዝቡ ፊት ክፉ ሆኖና እግዚአብሔር ትቶት ነው የሞተው። የቅናት ኃጢአት፣ ልክ ይቅር እንዳለማለት ሁሉ፣ በይበልጽ የሚጐዳው ከሚቀናበት ሰው ይልቅ የሚቀናውን ግለሰብ ነው።

ለምንድን ነው በቅናት ኃጢአት ላይ እግዚአብሔር የሚቆጣው? በሌላ መሪ ላይ መቅናትና በእነርሱ ላይ በክፉ መናገር ከእግዚአብሔርና ከዕቅዱ ጋር መጣላት ነው። መሪዎችን የሚያስነሣው፣ መንፈሳዊ ስጦታዎችንና ችሎታዎችን የሚሰጠውና በእነርሱ በኩል የሚሠራው እግዚአብሔር ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ የመምራት ኃይልና መሪ ለመሆን መመረጥ የሚመነጨው ከግለሰቡ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው። ስለዚህ፣ በመሪ ላይ በምናጉረመርምበት ጊዜ ሁሉ ወይም አመራሩን በማናቸውም መንገድ ከተቃወምን፣ እግዚአብሔርን በመቃወም እየሠራን ነው ማለት ነው። አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለን አመራር ደስተኛ ካልሆንን ወይም በሌላ ሰው የጸጋ ስጦታ የምንቀና ከሆነ፣ እግዚአብሔር ሲሠራ በመረጠበት መንገድ ላይ አጉረምርመናል ማለት ነው። ጳውሎስ እንዳለው፣ እንዴት ሸክላ በሠራው ሸክላ ሠሪ ላይ ያጉረመርማል? (ሮሜ 9:20-21) ዳዊት ከንጉሥ ሳኦል ጋር በነበረው ሁኔታ ይህንን ተረድቶ ነበር። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሆን ቢመርጠውም፣ ሳኦል ክፉ ንጉሥ ሆኖበት እንኳን ከንግሥናው ለማንሣት አልሞከረም። እግዚአብሔር ሳኦልን እንዳስነሣው ሁሉ እርሱ እስኪያወርደው ድረስ ዳዊት ጠበቀ። ለዳዊት ንጉሥ ለመሆን ሲል ሳኦልን መግደል በእግዚአብሔር ላይ ከማመፅ ጋር አንድ ነበር፣ ሳኦል በእግዚአብሔር የተቀባ ስለሆነ እግዚአብሔር እስኪያነሣው ጠበቀ (1ኛ ሳሙ. 24:1-15፤ 1ኛ ሳሙ. 26)።

ልንጠነቀቃቸው የሚገባ በርካታ የቅናት ዓይነቶች አሉ፡-



ሀ. በመሪነት ቦታ መቅናት። አንድ መሪ በቀላሉ የበላይ ሽማግሌ፣ የመዘምራን ቡድን መሪ፣ ወይም የሽማግሌዎች ጉባዔ ሰብሳቢ እንዲሆን ሌላ ሰው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሲመረጥ ሊቀና ይችላል። ሌላ ሰው ባለው የመሪነት ቦታ መቅናት እግዚአብሔር የፈለገውን ሰው በአመራር ላይ ለማስቀመጥ ያለውን መብት መጻረር ነው።

ለ. በሌላ ሰው የጸጋ ስጦታ መቅናት። መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም አማኞች መንፈሳዊ ስጦታን ይሰጣል (1ኛ ቆሮ. 12:7-11)። ነገር ግን እነዚያ መንፈሳዊ ስጦታዎች በዓይነት ይለያያሉ (ለምሳሌ፡- ማስተማር፣ ወንጌልን መስበክ፣ በልሳን መናገር)፣ እንዲሁም ስጦታዎቹ በደረጃ ይለያያሉ (ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ያለው የማስተማር ችሎታ ወይም የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ከሌለው ይለያል። አንዳንዶችን እግዚአብሔር በከፍተኛ ኃይል ይጠቀምባቸዋል፣ ሌሎቹን ደግሞ ከዚያ ባነሰ ኃይል ይጠቀምባቸዋል።) አብዛኛውን ጊዜ ከእኛ የሚበልጥ የጸጋ ስጦታ ባለው ሰው እንቀናለን። ተአምር በሚሠሩት ወይም፣ ጥሩ አድርገው በሚሰብኩት ወይም እኛ የተገለጠና ከእነርሱ በላይ ጐልቶ የሚታይ ጸጋ የሌለን ከመሰለንና እነርሱ ውጤታማ እንደ ሆኑ ስናስብ እንቀናለን። ከእኛ የበለጠ የጸጋ ስጦታ ባለው ሰው ላይ መቅናት በምን ዓይነት ሁኔታ ሊገለገልብንና ሊኖረን ስለሚገባው የጸጋ ስጦታ መጠን በሚወስነው መንፈስ ቅዱስ ላይ መነሣት ነው።

ሐ. በተለያየ የስኬት መጠን ላይ መቅናት። ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ ከሌላው ይበልጥ ስኬታማ ከሆነ ይቀናናሉ። አንደኛው ወንጌላዊ 100 ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ሲያመጣ ሌላኛው ወንጌላዊ 10 ብቻ ወደ ክርስቶስ ካመጣ፣ ውጤታማነቱ ዝቅ ያለው ሰው በቀላሉ ሊቀና ይችላል። ያንን ስናደርግ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 3:5-15 ላይ ያለውን ረስተናል። «አንዱ ይተክላል፣ አንዱ ያጠጣል የሚያሳድግ ግን እግዚአብሔር ነው።» ወይም አንድ

ሽማግሌ ሌላ ሽማግሌን ሕዝቡ አብልጦ ሲወድና ሰበሰጠ የመሪነት ቦታ ሲያጨው ሲቀና ይችላል። ብዙ ጊዜ ከቅናት የተነሣ የተሰያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሌላ መሪ ላይ ወሬ በማስወራት የሌላውን መሪ ሥራ ለማጥፋት ይሞክራሉ!

መ. እንደ ሌላ መሪ ታዋቂ ባለመሆን የተነሣ የሚመጣ ቅናት። በዋነኝነት ንጉሥ ሳኦልን ለቅናት ያነሣሣው ነገር ዳዊት ከእርሱ በላይ ታዋቂ በመሆኑ ነበር። የእስራኤል ሴቶች «ሳኦል ሺህ ገደለ፤ ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ ገደለ» (1ኛ ሳሙ. 18፡6-9) ብለው ሲዘፍኑ ሳኦል ዳዊትን በቅናት ዓይን እንደ ተመለከተው ተነግሮናል። የዚህ ዓይነት ቅናት በመሪዎች ዘንድ የተለመደ ነው። ሰዎች በተደጋጋሚ መሪውን ትተው የሆነ ለባኪ እንዲሰብካቸው ሲጠይቁ፣ ሰዎች ለአንድ መሪ ያላቸውን ፍቅር በግልጽ ሲያሳዩ፣ ወይም ለአንድ መሪ ዕውቅናቸውን ወይም አንድ ስጦታ ሲሰጡ፣ ወይም አንድ ሰው ዕድገትና የደመወዝ ጭማሪ ሲያገኝ ብዙ ጊዜ ሰይጣን እንዲህ ያለውን ሁኔታ በሌሎች ልብ ውስጥ ቅናትን ለመፍጠር ይጠቀምበታል። እኛ እንደ ሌሎቹ ዝነኛ ካልሆንን፣ ለዚህ ኃጢአት ፈቃድ እንዳንሰጥ ልንጠነቀቅ ይገባናል። ያንን ካደረግን፣ ያንን ሰውና በተሰየ ሁኔታ የቀባውን እግዚአብሔርን የሚቃወም ሥራ እንሠራለን። የምንጨነቀው በእርግጥ «ለእግዚአብሔር መንግሥት» እንጂ ለራሳችን ዝናና መንግሥት ካልሆነ፣ እግዚአብሔር ሌላ ሰውን በዚህ መንገድ በመጠቀሙ ልንደሰት ይገባል። አብዛኛውን ጊዜ ከሚቀናበት ሰው ይልቅ የሚጐዳው የሚቀናው ሰው ነው። ልክ ዳዊት ሁልጊዜም ዝነኛ እንደሆነው፣ ያ መሪም ዝነኛነቱ ይቀጥላል። ነገር ግን በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ሰላም አጥቶ የተጐዳውና በክፉ መንፈስ የተጨነቀው ቀናተኛው ሳኦል ነበር። በሌላ መሪ ዝነኛነት የተነሣ በልብህ ውስጥ ምሬት አለ? እግዚአብሔር እንደ አምላክነቱ የፈለገውን ሰው እንዲጠቀም እስካልፈቀድክ ድረስ ሰላም አይኖርህም። ኢየሱስ ያለውን አስታውስ። «ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ።» እግዚአብሔር



የሚሸልመው በዝነኝነት አይደለም። እርሱ የሚሸልመው በታማኝነታችን ነው። የሚያስፈልገው በምድር የሰዎችን ምስጋና መስማት ሳይሆን፣ በሰማይ የእግዚአብሔርን ምስጋና መስማት ነው።

ሠ. ይበልጥ በተማሩና ከእኛ በሚበልጥ ጸጋ በተሞሉ ወጣቶች መቅናት። ብዙ ጊዜ ያረጁ መሪዎች ይበልጥ የተማሩና በሚበልጥ የጸጋ ስጦታዎች የተሞሉ ወጣቶችን ይፈራሉ። እግዚአብሔር እነዚህን ወጣቶች አብልጦ ሲጠቀም ሲያዩ ቤተ ክርስቲያን እነርሱን ችላ ብላ ወጣቶቹን እንዳትመርጥ ይሰጋሉ። ብዙ ጊዜ እነዚህ ሽማግሌ መሪዎች «እነዚህ ወጣት መሪዎች ትዕቢተኞች ናቸው። ሁሉን ነገር የሚያውቁ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ምንም ነገር አያውቁም፣ ስለዚህ መሪ እንዲሆኑ አንፈቅድላቸውም።» ብለው ያስባሉ። የሚያሳዝነው፣ በዘመናችን፣ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን የሚወድዱና ሊያገለግሉት የሚፈልጉ ብዙ ወጣቶች ከቤተ ክርስቲያን የሚባረሩት በሽማግሌዎች ነው። ይህንን ስናደርግ ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ።

<u>አንደኛ፤</u> ብዙ ሽማግሌዎች መሪዎች ወጣት እያሉ እግዚአብሔር እንዴት ታላቅ በሆነ ኃይል እንደ ተጠቀመባቸው ረስተዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ታላላቅ መሪዎች ወጣቶች ነበሩ። ዮሴፍ የግብጽ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሲሆን በሠላሳዎቹ ዕድሜ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም፤ ኤርምያስ የነቢይነት ሥራውን የጀመረው በሠላሳ ዓመቱ ነበር፤ ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ ለሐዋርያነት ሲጠራ ገና በአሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ነበረ፤ እግዚአብሔር ጢሞቴዎስን ከጳውሎስ ጋር አድርጐ ቤተ ክርስቲያናትን ለመምራት ሲጠቀምበት ገና በሃያዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሽማግሌዎችን ብቻ አይደለም የሚጠቀመው። ወጣቶችንም ይጠቀማል። (ማስታወሻ፦ በሌላ በኩል ግን፣ ወጣቶች የተማሩ መሆናቸው የመሪነት ቦታን ሲያስጣቸው

እንደማይችል መረዳት አለባቸው። እግዚአብሔር ለመሪነት የሚያተኩርበት መሥፈርት መንፈሳዊ ብስለት ነው። እግዚአብሔር ወጣቶችንም ሽማግሌዎችንም ይጠቀማል። ዕድሜአቸው ከ80 በላይ የነበረውን ሙሴን፣ ኢያሱንና ካሌብንም ተጠቅሟል።)

ሁለተኛ፣ በዕድሜ የገፉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የተቀበሉ አዳዲስ አገልጋዮችን ሲቋቋሙ፣ የሚፈልጉት የእግዚአብሔርን መንግሥት ክብር ሳይሆን፣ የራሳቸውን ክብር ነው። እንደዚህ ያለ አመለካከት በልባችን ውስጥ ሲኖር፣ እየመራን ያለነው ለራሳችን ክብር መሆኑን አመልካች ነው። እየተጨነቅን ያለነው ለራሳችን ዝና ነው። እየገነባን ያለነው የእግዚአብሔርን መንግሥት ሳይሆን የራሳችንን ነው ማለት ነው።

አዎን፣ ወጣቶች ለመሪነት አስፈላጊ የሆኑ ልምዶች የሏቸውም። አዎን፣ በልባቸው ለእግዚአብሔር ከመስጠትና በእርሱ ከመደገፍ ይልቅ ብዙውን ጊዜ በትምህርታቸው ይኩራራሉ። እዎን፣ ከቀናኢነታቸው የተነሣ ስሕተት ይሠሩ ይሆናል። ግን እኛ ሽማግሌ መሪዎችስ ስሕተት እንሠራም እንዴ? እኛ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከባረርናቸው እግዚአብሔርን የማገልገል ልምድ ከየት ያገኛሉ? እኛ ከእነርሱ ጋር ጊዜን በማሳለፍ ካላስረዳናቸው በመንፈሳዊ ባሕርያት ማገልገልን ማን ያስተምራቸዋል? ከቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የተቀበሉትን ወጣቶች በሙሉ ካባረርናቸው የወደፊት መሪዎቻችን ከየት ይመጣሉ? በቅናት ተነሣስተን ወጣቶችን ከማባረር ይልቅ፣ ልክ ወጣቱን ሳውል ወስዶ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲበስል እንዳደረገው በርናባስ ማድረግ እጅግ የተሻለ ነው። ማን ያውቃል ምናልባትም እኮ ብዙ ወጣቶች በኋላ ጳውሎስ እንደተባለው ሳውል እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል ሊጠቀምባቸው ይችል ነበር? ነገር ግን እኛ መሪዎች ስለ ፈራናቸውና ስለ ቀናንባቸው ብቻ ከቤተ ክርስቲያናችን አባርረናቸዋል።

ስንቀና፣ በእግዚአብሔር ላይ እያጉረመረምን፣ ጌትነቱን እየተቃወምን እና እርሱ በፈቀደው መንገድ የመሥራት መብቱን እየገደብን ነው። ለመሪነት የሚፈልገውን ማንኛውም ሰው የማስነሣት መብት አለው። ለፈለገው አማኝ የፈለገውን ዓይነት መንፈሳዊ ስጦታ የመስጠት መብት አለው። እርሱ በፈለገው ሰው ላይ በኃይል የመሥራትና ባልፈቀደው ሰው ደግሞ በትንሽ የመሥራት መብት አለው። እርስ በርስ በመቀናናት ከእግዚአብሔር ጋር ትጣላለህ? አንተ ሸክላ እግዚአብሔር ደግሞ ሸክላ ሠሪ መሆኑን ረስተሃል? በዚህ በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ኃጢአት እግዚአብሔር እንዳይፈርድብህ ተጠንቀቅ።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እነዚህን ልዩ ልዩ የቅናት ዓይነቶች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንዳየህ አብራራ። ለ) ቅናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ውጤት ያስከትላል? ሐ) ሰዎች እርስ በርስ የሚቀናኑበትን ምክንያት ዘርዝር? መ) ምንድን ነው ስለ እግዘአብሔርና የፈለገውን ሰው ስለ መጠቀም መብቱ የረሱት? ሠ) ልብህን ፈትሽ። የምትቀናበት ሰው አለ? ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ጌትነት የመቋቋም ኃጢአትህን ተናዘዝ። |

## 2. ከተራ አማኞች በጣም የበለጥን እንደ ሆንን የማመን ኃጢአት።

የመድኃኒቱ ዓለም እንደ ኤድስ ያሉ በርካታ በሽታዎች የሚመነጩት ቫይረስ በሚባሉ ትንንሽ ሕዋሳት መሆኑን ደምድመዋል። ቫይረሶች በጣም ትንንሽ ከመሆናቸው የተነሣ እነርሱን ለማየት ኃይለኛ ማይክሮስኮፕ ያስፈልጋል። ቫይረሶች ያስማቋረጥ ስለሚቀያየሩ ዶክተሮችን ተስፋ ያስቆርጣሉ። አንድን ቫይረስ ለማጥፋት መድኃኒት ሲሠራ፣ ያ ቫይረስ ራሱን ስለሚለውጥ መድኃኒቱ አዲሱን ዓይነት ቫይረስ መግደል አይችልም። ይህም በመሪ ልብ ውስጥ ካለ ትዕቢት ጋር ተመሳሳይ ነው። አንድ ዓይነት ትዕቢትን ስናሸንፍ፣ ትዕቢት በሌላ መልኩ ይገለጣል። ትዕቢት በመሪ ልብ ውስጥ ራሱን ከሚገልጥባቸው መንገዶች አንዱ ስለ ቤተ ክርስቲያን አባላት ያለን አመለካከት ነው። አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በልባቸው የቤተ

ክርስቲያን አባላትን ይንቃሉ። አንዳንድ መሪዎች በሚከተሉት መንገዶች ከቤተ ክርስቲያን አባላት የተሻሉ እንደ ሆኑ ያስባሉ፡-

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነርሱ ብቻ መንፈሳዊ እንደ ሆነ ማሰብ ይጀምራሉ። እነርሱ ብቻ ጥሩ አድርጎ መጸለይና መስበክ፣ ወዘተ. . . የሚችሉ ይመስላቸዋል። እነርሱ ብቻ ለእግዚአብሔር ዋጋ የሚከፍሉ ይመስላቸዋል። ራሳቸውን ቅዱስ አድርገው በመገመት፣ አብዛኛዎቹ አባላት ኃጢአተኞችና ከዓለም መለየት ያቃታቸው አድርገው ያስባሉ።

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት እግዚአብሔርን ማገልገል እንደማይፈልጉና እንዴት ማገልገል እንደሚቻል እንደማያውቁ ያስባሉ። «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኛ ብቻ ነን የምናገለግለው» ብለው ያጉረመርማሉ። «ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለእግዚአብሔር እንዲሠሩ ብንፈቅድ፣ ነገሮችን ያበላሻሉ። ስለ እግዚአብሔር በቂ እውቀት የላቸውም። ስለ ወንጌል በቂ እውቀት የላቸውም። ሥሩ የምንላቸውን በደንብ አይሠሩም። ስለዚህ ይህን ሁሉ ማድረግ የሚጠበቀው ከእኛ ነው» ይላሉ። ከዚህ የተነሣ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን ለኃላፊነት መጋበዝን አሻፈረኝ ይላሉ። ሰዎችም ሁሉን ነገር እነርሱ ማድርግ እንዳለባቸው ያስባሉ። ከዚህ አመለካከት ከመጡ አሳዛኝ ውጤቶች ውስጥ አንዱ የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚህ ትምህርት ማመኑ ነው። ሰዎች ተራ አባል በመሆናቸው ምንም ማድረግ እንደሌለባቸው ያስባሉ። ስለዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ፣ ይዘምራሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ሲጠቀምባቸው እንደሚችል ምንም ሳይጠብቁ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ሰዎች ስለ ክርስቶስ ለማወቅ ወደ እነርሱ ሲመጡ፣ «እኔ ወደ ክርስቶስ ልመራህ አልችልም። ይህንን የሚያደርገው ወንጌላዊው መሆን አለበት።» ይላሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር ብዙ የጸጋ ስጦታዎች የሰጣቸው በርካታ የቤተ ክርስቲያን አባላት እግዚአብሔርን አያገለግሉም። የቤተ ክርስቲያን



መሪው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉን ነገር እንዲያደርግ በመጠበቅ ንቁ ሳይሆኑ ይቀራሉ።

ሐ. የቤተ ክርስቲያን አባል የማገልገል ፍላጎት ሲኖረውና ለእግዚአብሔር ሲቀና፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥረቱ ይሳለቃሉ። «ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለመጀመር ማን ፈቀደልህ? ከጐዳና ተዳዳሪ ልጆች ጋር መሥራት ምን ይጠቅማል፤ ለቤተ ክርስቲያን ምን ይጠቅማሉ?» ይላሉ ተስፋ በመቁረጥ።

መ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ ሰዎች እነርሱ ያላቸው ዓይነት የትምህርት ደረጃ ስለሌላቸው እንደማይጠቅሙ ያስባሉ። «እነዚህ ሰዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? በየእሑዱ ከመምጣትና ከመዘመር ሌላ እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው ይችላል ብለን ልንጠብቅ አንችልም። እነርሱ ድሃ፣ ያልተማሩና የማይጠቅሙ ናቸው። እግዚአብሔር ለሥራው እኛን መጠቀሙ ጥሩ አይደል? ሥራውን ለመሥራት እኛ የተማርነውና ሐብታሞቹ ባንኖር ኖሮ ይህች ቤተ ክርስቲያን የት ትደርስ ነበር?» እንላለን በልባችን።

መሪ እንደ መሆናችን መጠን ስብከታችንን መስማት አለብን ብለን እናስባለን። አብዛኛውም ጊዜ ይህ በልባችን ያለውን ኩራት ያሳያል። ምን ያህል ነው በስብከታችን ላይ መሪ በመሆናችን ብዙ ብንሰጥም ሕዝቡ ግን አይሰጥም፣ ወይም እኛ ቅዱሳን ብንሆንም ሕዝቡ ቅድስና ይጎድላቸዋል፣ ወይም እኛ በትጋት የእግዚአብሔርን ቃል ብናጠናም ሕዝቡ ግን አያጠናም፣ ወዘተ. . . ብለን የተናገርነው። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ባልተማሩ ወይም ትንሽ ተሰጥኦ ባላቸውና እኛ በምንንቃቸው ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንደሚሠራ መርሳት እንዴት ቀላል ነው (1ኛ ቆሮ. 1:18-29)። ወደ ኢትዮጵያ ወንጌልን ያመጡት አብዛኛዎቹ የወንጌል መልእክተኞች (ሚስዮናውያን) በአሁን ዘመን ካለነው አብዛኞቻችን ጋር ሲነጻጸሩ ያልተማሩ ነበሩ። የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያንና አሁን እንኳን ያሉት አብዛኛዎቹ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የመሠረተባቸው ወንጌላውያን ከእኛ ጋር ሲነጻጸሩ ያልተማሩ ነበሩ።

በዛሬ ዘመን ከተደረጉ ትልልቅ ሥራዎች ውስጥ አብዛኛው እኛ በምንንቃቸው ሰዎች የተሠራ ነው። ስለዚህ ከዚህ የትዕቢት ኃጢአት መጠንቀቅ አለብን።

22ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን አባላት የተሻልን ነን ብለው የሚያስቡባቸውን መንገዶች ግለጽ? ለ) በአመራራቸው ላይ ይህንን የበላይነት መንፈስ እንዴት ነው የሚያሳዩት?

23ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 15:23-32፤ ሉቃ. 13:14-17ን አንብብ። ሀ) ኢየሱስ የሃይማኖት መሪዎችን የከሰሰበት ኃጢአት ምንድን ነው? ለ) እንደዚህ ያለ ኃጢአት በዘመናችን ያሉ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እንዴት ነው የሚፈታተነው? በመሪዎች ሕይወት ይህንን ኃጢአት እንዴት እንዳየህ መግለጫ ስጥ። ሐ) ኢየሱስ እንደ ዝሙት ባሉ ሌሎች ኃጢአቶች የተቆጣ ላይመስል በዚህ ኃጢአት ላይ ግን በጣም የተቆጣው ለምንድን ነው?

### 3. ግብዝነት:- መንፈሳዊ የመምሰል ኃጢአት።

ለቤተ ክርስቲያን መሪ አደገኛ ከሆኑ ኃጢአቶች መካከል አንዱ መንፈሳዊ የሚመስል ነገር በማድረግ የሰዎችን ትኩረትና አክብሮት ለማግኘት መፈለግ ነው። ስለዚህ በአምልኮአችን መንፈሳዊ ለመምሰል እንሞክራለን ወይም ሕይወታችንና ለእርሱ ያለን ፍቅርና አገልግሎት መመስከር ሲገባው ስለ ራሳችን ብዙ ለመናገር እንሞክራለን። ኢየሱስ ይህንን ኃጢአት «ግብዝነት» ይለዋል። ከሃይማኖት መሪዎች ሕይወት አምርሮ የነቀፈውም ይህንኑ ነው።

ሁላችንም በመንፈሳዊነታችን መታወቅ እንፈልጋለን። ይህ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን መሪ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም መንፈሳዊ ኑሮን በተመለከተ ለሌሎች ምሳሌ መሆን እንፈልጋለን። ነገር ግን እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው የመሆን ይህ ፍላጐታችንን ሰይጣን ለክፋት ሊጠቀምበት ይችላል። ፈጥነንም በግብዝነት ኃጢአት እንወድቃለን።

(ማስታወሻ:- በግሪክ ቋንቋ፣ «ግብዝነት» የሚለው ቃል የመጣው «መተወን» ከሚለው ቃል ነው። በድራማ ውስጥ ሰዎች



ያልሆኑትን ሆነው ለሚጫወቱት ገጸ ባሕሪ የሚሠራ ቃል ነው። ስለዚህ ግብዝነት ማለት ያልሆነውን ለማስመሰል መሞከር ማለት ነው።)

ግብዝነት አብዛኛውን ጊዜ የሚታየው በሰው ፊት በሚያገለግሉ ሰዎች (ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ በሰባኪዎች፣ በወንጌላውያን፣ በመዘምራን ቡድን አባላት ነው)። ዝማሬውን ለመምራት፣ ለመስበክ፣ ለማስተማርና ለመጸለይ፣ ወዘተ. . . በሕዝብ ፊት እንቆማለን። ሰይጣን አብዛኛውን ጊዜ በልባችን በምናደርገው ነገር ሌሎችን ለማስገረም አንድንጥር ያደርገናል። ግብዝ የምንሆነው ሌሎችን ለማስደነቅ ስንል ያልሆነውን ለመሆን ወይም በተፈጥሮአችን የማናደርገውን ነገር ለማድረግ ስንሞክር ነው። መንፈሳዊ መስሎ የመታየት ኃጢአት ወይም እውነተኛ መንፈሳዊ ከመሆን ይልቅ በሰዎች ዓይን ልዩ ሆኖ ለመታየት መሞከር በመሪዎች ፊት የተጋረጠ አደገኛ ኃጢአት ነው።

የግብዝነት ኃጢአት ሥር ሥራችን ሳይሆን፣ አንድ ነገር የምናደርግበት ምክንያት ነው። የምንጸልይበት ወይም የምንሰብክበት ወይም የምንዘምርበት መንገድ መንገድ ሳይሆን፣ ይህንን የምናደርግበት ምክንያት ነው። በቤተ ክርስቲያን መሪ ሕይወት ውስጥ ከልባችን ያልሆነውን መንፈሳዊ ለመምሰል የምንጥርባቸው ብዙ ክፍሎች አሉ:-

ሀ. የጉባኤ ጸሎት:- በጉባኤ መካከል ስንጸልይ ሰዎች መንፈሳዊ ነው ብለው እንዲያስቡን ለማድረግ ስንል ለራሳችን በማንጸልይበት መንገድ ከጸለይን፣ የግብዝነት ኃጢአትን ሠርተናል ማለት ነው። ይሄ ምናልባትም ጮክ ብሎ መጸለይ፣ በርካታ «ሃሌሉያዎችን» ወይም «አሜኖችን» መጠቀም፣ ድምጾችን እንዲያስገመግም ማድረግ፣ ማልቀስ፣ እየተንቀጠቀጡ መጸለይ፣ እና የመሳሰሉት ሊሆን ይችላል። ሌሎች ይህንን ሲያደርጉ አይቶ መንፈሳዊ ለመምሰል መኮረጅም ግብዝነት ነው።

ለ. ስብከት:- ግብዝነት ብዙ ጊዜ በስብከታችን ውስጥ ይታያል:: ምሳሌ፣ ታዋቂ ሰባኪን በመኮረጅ ጮክ ማለት፣ ማልቀስ፣ አስደናቂ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ፣ ወዘተ. . . ግብዝነት ነው:: በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ብንሰብክ የማናደርገውን ነገር እንደምናደርግ ማስመሰልም ግብዝነት ነው:: ለምሳሌ፣ ስለ ጸሎት አስፈላጊነትና ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ስለ ማጥፋት አስፈላጊነት ስንሰብክ፣ እኛ ራሳችን ግን በሥራ ከመወጠራችን የተነሣ የጸሎት ጊዜ ከሌለን፤ ወይም ስለ ቤተሰብ የጥሞና ጊዜ አስፈላጊነት ስናስተምር፣ በቤታችን ግን የጥሞና ጊዜ ከሌለን፤ ወይም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና አስፈላጊነት እያስተማርን፣ እኛ ግን መጽሐፍ ቅዱስን የማናጠና ከሆነ ማለት ነው::

ሐ. በመዘምራን ቡድን ውስጥ መዘመር:- በሰዎች ፊት መንፈሳዊ ለመምሰል ስንል ዓይናችንን ጨፍነን የምንጸልይ ከሆነ፣ ወይም ከሌላ ቤተ ክርስቲያን የመጡ የመዘምራን ቡድን አባላት በስሜት መሬት ላይ ሲወድቁ ስላየን ብቻ በቤተ ክርስቲያናችን የሚገኙ ሰዎችን ለማስገረም ብቻ ያንን ማድረግ ከጀመርን ግብዝነት ነው::

ታዲያ እነዚህ ሁሉ ተግባራት ከልባችን የምናደርጋቸው ከሆነ የተፈቀዱ እንደ ሆኑ ማወቁ አስፈላጊ ነው:: ግን 1) በልባችን ያንን የምናደርገው ሰዎችን በመንፈሳዊነታችን ለማስገረም ከሆነ፣ ወይም 2) የሌሎችን ድርጊት የምንኮርጅ ከሆነ፣ ወይም 3) በምንለውና በአኗኗራችን መካከል ልዩነት ካለ፣ ያኔ በግብዝነት ኃጢአት ወድቀናል ማለት ነው:: ብዙ ጊዜ ሰዎች ግብዝ መሆን አለመሆናችንን ላያውቁ ይችላሉ:: እኛና እግዚአብሔር ብቻ ተግባራችን እውነት እንደ ሆነ ወይም በሌሎች ፊት መንፈሳዊ መስሎ ለመታየት እንደ ሆነ እናውቃለን::

> 24ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች መንፈሳዊ እንደሆንክ እንዲያስቡ ለማድረግ ስትል ሌሎችን የኮረጅክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በግብዝነት ኃጢአት እንዴት እንደሚወድቁ ሌላ መግለጫ ስጥ:: ሐ) አንድ



> የቤተ ክርስቲያን መሪ ያልሆነውን ለመምሰል ከመሞከር ይልቅ በመንፈሳዊነቱ እውነተኛ መሆኑን ለማሳየት ምን ማድረግ አለበት?

## 4. በጣም በሥራ ከመወጠራችን የተነሣ ለቤተሰባችን ተገቢውን ትኩረት ያለመስጠት ኃጢአት::

> 25ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ሳሙ. 2:12-36ን አንብብ:: ሀ) እግዚአብሔር ለምንድን ነው በዔሊ የተቆጣው? ለ) ትንቢቱ እንዴት ነው የተሳካው? ሐ) ይህ ምዕራፍ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልጆቻቸውን እግዚአብሔርን ስለ መታዘዝ ማስተማር እንደሚገባቸው ምን ያስተምራል?

ለአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ያሉበትን ኃላፊነት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መወጣት ነው:: ብዙ ጊዜ የመንግሥት ሥራ ኃላፊነት ወይም የሙያ ኃላፊነት ይኖርበታል:: ቤተሰቡን የማገልገል ኃላፊነትም ይኖርበታል:: በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም ኃላፊነት አለበት:: አንድ መሪ እነዚህን ዋና ዋና ኀላፊነቶችን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ካላካሄደ፣ ፈጽሞ ውጤታማ መሪ አይሆንም::

የሚያሳዝነው ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ከሦስቱ የኃላፊነት ክፍሎች ውስጥ፣ ሚዛናዊ ባለመሆናችን የተነሣ አብልጦ የሚጐዳው ቤተሰባችን ነው:: አንድ መሪ ሥራው በደንብ ካልሠራ፣ ሥራውን ሊያጣ ወይም ለመኖር የሚበቃ ገንዘብ ላይኖረው እንደሚችል ያውቃል:: ስለዚህ መሪ ለዚህኛው ሕይወቱ ክፍል በቂ ጊዜ ይሰጣል:: የቤተ ክርስቲያን መሪ በማያቋርጥ ሁኔታ እርዳታ ፈልገው ወደ እርሱ የሚመጡ ብዙ ሰዎች አሉ:: እስከ ማታ ድረስ የሚቀጥሉ ስብሰባዎችም ይኖራሉ:: አንድ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች መሪ ማድረግ አለበት ብለው የሚያምኑትን ሁሉ ለማድረግ የሚበቃ ጊዜ የለውም:: ስለዚህ መሪ የበለጠ መሥራት የሚችልበትን ጊዜ ከየት ያመጣል? ከቤተሰቡ ጋር ከሚያሳልፈው ጊዜ ላይ መቀነስ አለበት:: ቤተሰቡ ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብ በግልጽ ጊዜህን እንፈልገዋለን ብለው አይጫኑትም:: ደግሞም አያጉረመርሙም፣ ምክንያቱም ማጉረምረም

እንዳለማክበርና ሰዎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለው የሚያስቡትን ነገር እንደ መቃወም ስለሚታይ ነው። ስለዚህ አብዛኛ ዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚሠሩት ኃጢአት በቤተሰባቸው ላይ ነው። ያም ከቤተሰብ ጋር በቂ ጊዜ ያለማሳለፍ፣ የሚያስፈልጋቸውን ያለማሟላትና እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ያለማስተማር ኃጢአት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ መሪዎች ቤተሰባቸውን ችላ ሲሉ፣ በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ ጥፋት እንደሚያስከትሉ ያስተምራል። ዔሊ እግዚአብሔርን የሚወድና በሊቀ ካህንነትም የሚያገለግል ነበር። ነገር ግን ልጆቹ መንፈሳዊ እንዲሆኑና እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ፈጽሞ አላስተማራቸውም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሊቀ ካህንነቱን ለሳሙኤል ሰጠው። በድጋሚ፣ ሳሙኤልም በጣም በአገልግሎት የተወጠረ ሰለ ነበረ ልጆቹን እግዚአብሔርን እንዲወድዱና እንዲታዘዙ አላስተማራቸውም (1ኛ ሳሙ. 8:3)። ስለዚህ ልጆቹ መሪ እንዳይሆኑ ተናቁ። ሌላው ቀርቶ በጣም መንፈሳዊ የነበረው ንጉሥ ዳዊትም እንኳ ልጆቹን ችላ በማለቱ በኋለኛው ዘመን ትልቅ የልብ ሥቃይ ፈጥሮበታል።

ልጆቻችን ትንንሽ እያሉ፣ ይህ ኃጢአት ብዙ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው አይመስልም። ሥራ ለመሄድ ጠዋት ልንወጣና ከቤተ ክርስቲያን ስብሰባ በጣም አምሽተን ልንመለስ እንችላለን። ያንን ስናደርግ፣ ልጆቻችን በአፍላ ዕድሜአቸው ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና እርሱን ስለ መታዘዝ ለማስተማር የሚያስችል ግንኙነት ሳይኖረን ይቀራል። ሳይንቲስቶች እንደሚናገሩት በልጆቻችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ልናመጣ የምንችለው እስከ 10 ዓመታቸው ድረስ ነው። ከዚያ በኋላ፣ የልጁን ባሕሪ እንደ ልብ ማስተካከል ያዳግታል። ከዚያ በኋላ፣ ልጆች ምክር ለማግኘት ከቤተሰቦቻቸው ይልቅ ጓደኞቻቸውን ይመርጣሉ። ልጆቻችን ካደጉ በኋላ አባታቸው ከእነርሱ ጋር ለመሆን ጊዜ ባለመውሰዱ መራራ ሆነው ያድጋሉ። እግዚአብሔርን ከመውደድ ይልቅ፣ አባታቸውን ስለ ወሰደባቸው



እግዚአብሔርን ይወቅሳሉ። ቤተ ክርስቲያን የአባታቸውን ጊዜና ትኩረት ሁሉ በመውሰዷ የተነሣ ቤተ ክርስቲያንን ይንቃሉ። አንድ ጊዜ ይህ ምሬት በልባቸው ከገባ፣ ወላጆች ዳግም የልጆቻቸውን ልብ ማሸነፍና እግዚአብሔርን እንዲወድዱ ማድረግ ይከብዳቸዋል። በቀሪው ሕይወታቸው ዘመን ሁሉ፣ እነዚህ ወላጆች ልጆቻቸው ከእግዚአብሔር ሲሸሹና ቤተ ክርስቲያንን ሲጠሉ የማየት መራራ ጽዋ ይጠብቃቸዋል።

ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ላይ እንደሚያስጠነቅቀን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወታቸውን ሚዛናዊ በሆነ መልክ የሚመሩና ለቤተሰባቸው በቂ ትኩረት የሚሰጡ መሆን አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው ሚስቱንና ልጆቹን መንከባከብ አለበት። እነርሱን ስለሚወዳቸው፣ እግዚአብሔርን ችላ ከማለት ይልቅ፣ ልጆቹ በለጋ ዕድሜአቸው እግዚአብሔርን መውደድና መታዘዝ ይለምዳሉ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆናችን መጠን፣ ከልጆቻችን ጋር ጊዜ የምናሳልፍበትን ጊዜ ሚዛናዊ ማድረግን መማር አለብን። ይህ ማለት:-

ሀ. አባት እንደ መሆናችን መጠን፣ የልጆቻችንን ጉዳይ የመከታተል የግል ፍላጐት ሊኖረን ይገባል። ገና በለጋ ዕድሜአቸው እግዚአብሔርን መውደድ ልናስተምራቸው ይገባል። ልጆች የቤተ ክርስቲያን መሪ ቤት «ውስጥ» ስላደጉ ብቻ እግዚአብሔርን መፍራትን ተምረው ያድጋሉ ማለት አይደለም። ይልቁንም፣ አባትየው በማስተዋል ሊያስተምራቸው ይገባል። ይህ ማለት በአባትና በልጅ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ባህላችን የሚያስተምረውን ልንለውጥ ይገባል ማለት ነው። «ልጆቹን የማሳደግና ስለ እግዚአብሔር የማስተማር ኃላፊነት የሚስቱ ነው» ማለት የለብንም። ይልቁንም እንደ ራሳችን ኃላፊነት እናየዋለን። ልጆቻችንን ዝም ብለው ከጐረቤት ልጆች ጋር መንደር ውስጥ እንደ ፈለጉ እንዲሯሯጡ አንለቅቃቸውም። ልጆቻችን እንደ

ጉረቤት ልጅ እንደ ፈለጉ ከሚሆኑ ይልቅ እግዚአብሔርን እንዲወዱ በማስተዋል አብረናቸው እንሠራለን።

ለ. ልጆቻችንን ገና በለጋ ዕድሜአቸው ልናስተምራቸው እንጂ እስኪያድጉ ልንጠብቅ አይገባም። ከፍ ካሉ ልጆች ይልቅ ትንንሽ ልጆች ይበልጥ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል። ገና ለጋ እያሉ ነው አብዛኛው ባሕሪያቸውና አመለካከታቸው የሚቀረጸው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪ ትንንሽ ልጆች ባሉት ልጆች እግዚአብሔርን እንዲወድዱ ለማስተማርና ከእነርሱ ጋር ጊዜ ያሳልፍ ዘንድ ከቤት ውጪ ያሰውን ጊዜውን መገደብ አለበት። ነገር ግን ካደጉ በኋላ፣ አብዛኛውን ጊዜውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጠት ይችላል።

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪው ተቀዳሚ ኃላፊነት ቤተሰቡን መንከባከብ ነው። ሁለተኛው ኃላፊነቱ ለቤተ ክርስቲያን ነው። እነዚህን በማገላበጥ ቅድሚያ ትኩረታችንን ለቤተ ክርስቲያን በመስጠት ለቤተሰባችን ዝቅተኛ ትኩረት ልንሰጥ አይገባም። ልጆቹ ካደጉ በኋላም እንኳ፣ የቤተሰቡ ፍላጐት ከቤተ ክርስቲያን ፍላጐት ጋር የሚጋጭበት ጊዜ ይኖራል። ልጆቹ ሊረዱ ከሚችሉት ድንገተኛ ጉዳይ ውጪ፣ መሪው ከቤተ ክርስቲያን ሥራ ይልቅ ቤተሰቡን ሊመርጥ ይገባል።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና አገልጋዮች ልጆቻቸውን ችላ ከማለታቸው የተነሣ ልጆቻቸው እግዚአብሔርን የማይወዱ ሲሆኑ እንዴት እንዳየህ ግለጽ። ለ) አባት ለልጆቹ ስሚጫወተው ሚና በባሕላችን ካሉ መረዳቶች የትኛዎቹ መቀየር አለባቸው? ሐ) ሽማግሌዎች በዚህ መንገድ ኃጢአት እንዳይሠሩ ለማድረግ የትኞቹ የቤተ ክርስቲያን አመለካከቶች መቀየር አለባቸው? |
| 27ኛ ጥያቄ:- 2ኛ ሳሙ. 11ን አንብብ። ሀ) ዳዊት የሠራው ኃጢአት ምንድን ነው? ለ) ዳዊት ኃጢአቱን የፈጸመው አዲስ መሪ እያለ ነው ወይስ ለረጅም ጊዜ መሪ ከሆነ በኋላ ነው? ሐ) ለምን ይመስልሃል ዳዊት በዚያ የሕይወቱ ምዕራፍ ለዚያ ኃጢአት የተጋለጠው? መ) ስለ መሪና ስለ ዝሙት ኃጢአት ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን? |



## 5. ዝሙት:- ለባለቤታችን ግብረ ሥጋን በተመለከተ አለመታመን።

መጽሐፍ ቅዱስ ከትዳር ውጪ ያለ ማንኛውም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምረናል። ይህም ከማግባታችን በፊት የሚፈጸም የዝሙት ኃጢአት ሊሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ይህ ኃጢአት «መሴስን» ይባላል። ወይም ካገባን በኋላ፣ ከባለቤታችን ውጪ የምንፈጽመው ደግሞ ዝሙት ይባላል።

ሰይጣን በርካታ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከሚያሸንፍበትና የቤተሰባቸውን ግንኙነትና ዝናቸውን ከሚያበላሽባቸው ነገሮች አንዱ የዝሙት ኃጢአት ነው። ወይም መሪዎች ዝሙት ባይፈጽሙም እንኳን፣ ሰዎች ዝሙት የፈጸሙ በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ካለፉ፣ መሪዎች መልካም ዝናቸውን ሲያጡ ይችላሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆናችን መጠን፣ ራሳችንን ዝሙት ከመሥራት ወይም ዝሙት በመሥራት ሊያስጠረጥር ከሚችል ሁኔታ መጠበቅ አለብን።

ከብዙ ዓመታት በፊት ዝነኛ የሆነ ሰባኪ ዝሙት መሥራቱን በሚያስጠረጥር ሁኔታ ውስጥ ራሱን አገኘ። በሆነ ጉዳይ ላይ ልታማክረው እንዲት ያሳገባች ሴት ወዳረፊበት ሆቴል ትመጣለች። ወዲያውኑ ይህቺ ሴት ያረፊበትን ሆቴል ክፍል ለቅቃ ስትወጣ ሰዎች ዝሙት ሠርቷል ብለው ሊጠረጥሩት እንደሚችሉ ገመተ። ስለዚህ አብሮት ከሚሠራው ሰው ጋር አንድ ቃል ገባ። አንድ ሴት በጣም ወደ እርሱ ስትቀርብ ካዩ ወይም ከሆነች ሴት ጋር ብዙ ጊዜ ካጠፉ ወዲያውኑ ፊት ለፊት እንዲገሥጹትና ነገሩ እስኪቀየር ድረስ ያንን እንዲያደርጉ ተስማማ። ወይም የሚያውቋት ሴት እነርሱ ባረፉበት ሆቴል ካረፈች ሰዎች የሆነ ግንኙነት አላቸው ብለው ስለሚጠራጠሩ ወዲያውን ሌላ ሆቴል እንዲቀይሩ ተስማሙ። ይህ ወንጌላዊ አገልግሎቱ በዝሙትም ሆነ በዝሙት ኃጢአት በመከሰስ

እንዲበላሽ አልፈሰገም። አሁን ከ50 ዓመታት በኋላ እንኳን ያሰውን መንፈሳዊ ዝና እንደ ጠበቀ ሲሆን፣ በአማኞችም ሆነ ባላመኑት ዘንድ በቅንነት እንደሚኖር ይታወቃል።

መሪዎች ብዙ ጊዜ ዝሙት ሊሠሩ በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። <u>አንደኛ</u>፡- ብዙ ጊዜ ለአገልግሎት ብቻችንን እንጓዛለን፤ ብዙ ፈተና ያሰበት ሆቴል ውስጥም እናርፋለን። ከሴተኛ አዳሪ ጋር ዝሙት ብንፈጽም ማንም አያውቅብኝም ብለን እናለባለን። በቀላሉ ልንፈተንና ልንወድቅ እንችላለን። ማንም በማያውቀን ቦታ ስናርፍ፣ በዝሙት ኃጢአት የመፈተን ዕድላችን የሰፋ ነው። <u>ሁለተኛ</u>፣ ብዙ ጊዜ ከመሪው ጋር ለመሆንና ከእርሱ ጋር በመሆን የእግዚአብሔርን የኃያልነት ስሜት እንዲሰማቸው ሊሉ ቆንጆ ሴቶች የቤተ ክርስቲያን መሪውን ይቀርቡታል። <u>ሦስተኛ</u>፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎታቸውና በማማከር ጊዜያቸው ያሰማቋረጥ ከሴሎች ሴቶች ጋር ይገናኛሉ። ይህ ደግሞ አካላዊና ስሜታዊ መሳሳብን ሊፈጥር ይችላል። ይህ በተለይም የመዘምራን ቡድን አባላት ዝማሬ ለመለማመድና ለአገልግሎት አብረው ብዙ ሰዓታት ስለሚያሳልፉ ይከሰታል። ካልተጠነቀቁ በስተቀር፣ ሰይጣን ይህንን ተጠቅሞ ወደ ዝሙት ኃጢአት ሊወስዳቸው ይችላል።

በማቴ. 5:27-28 ላይ ኢየሱስ ዝሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በተመለከተ አለመታመን ብቻ እንዳልሆነ ያስጠነቅቃል። ኢየሱስ ሲናገር፣ «አትመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል» ብሏል። ስለዚህ የዝሙት ኃጢአት ሌላ ሴትን በተመለከተ ንጹሕ ያልሆነ ማለብንም ይጨምራል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪ አካሉን ብቻ ሳይሆን፣ አሳቡንም ከዝሙት መጠበቅ አለበት። ይህ ማለት አንድ መሪ በአሳቡ ዝሙትን ሊያስብ ከሚችልበት ሁኔታ ራሱን ነፃ ማድረግ አለበት ማለት ነው። ይህም ቆንጆ ሴትን ለረጅም ጊዜ አትኩሮ ማየት ሊሆን ይችላል። ወይም



ሌሎች ሴቶች በሚታጠቡበት ወንዝ ውስጥ ገብቶ መታጠብና ከዚህም የተነሣ አዕምሮ መጥፎ ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት አዕምሮአችን ዝሙትን እንዲያስብ ሊያደርጉ የሚችሉ የቪዲዮ ፊልሞችን ወይም መጽሔቶችን ካለማየት በመጠንቀቅ ሊሆን ይችላል።

ታዲያ ራሳችንን ከዝሙት ኃጢአት ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብን?

ሀ. ከባለቤትህ ጋር ጥሩ የሆነ ስሜታዊና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊኖራችሁ ይገባል። ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኃጢአት የሚወድቁት በቤታቸው የሆነ ችግር ካለና የቅርብ ጓደኛ ፍላጎታቸው በማይሟላበት ጊዜ ነው። በ1ኛ ቆሮ. 7:1-5 ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዝሙት ኃጢአት እንዳይፈተኑ ከሚስታቸው ጋር ጥሩ የሆነ ጾታዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስጠነቅቃል።

ለ. አገልግሎትህ ለረጅም ጊዜ ከባለቤትህ እንዲለይህ አትፍቀድ። እነርሱ በሌላ ቦታ ሚስታቸው ደግሞ በሌላ ቦታ ከመኖራቸው የተነሣ በዝሙት ኃጢአት የሚፈተኑ በርካታ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አሉ። ይህ ደግሞ ባልየውንም ሆነ ሚስትየውን ለዝሙት ኃጢአት ያጋልጣል። እንደዚህ ያለው የባልና ሚስት ለረጅም ጊዜ መለያየት የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ በጣም ያጠራጥራል። ሚስትየው ከባሏ ጋር ለአገልግሎት አብራው ባለመሄዷ በዝሙት ቢወድቅ፣ እርሷ በከፊል ልትወቀስ ይገባል። ማንኛውም ወንጌላዊ ለአገልግሎት ወደ አንድ ቦታ ሲሄድ ከባለቤቱ ጋር ካልሄደ እምነቱን እንደማያጓድል ያስባል። ራሱንና ሚስቱን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እየጨመረ ነው። የጾታ ግንኙነት የማድረግ ተፈጥሮአዊ ፍላጎት በቀላሉ ሊያይልባቸው ይችላል። ይህ ኃጢአት በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባውን የመንፈስ አንድነትና ደስታ ያጠፋል፣ በተጨማሪም ባልየው በቤተ ክርስቲያን ያለውን አገልግሎት ሊያሳጣው ይችላል።

ሐ. ለዝሙት ሊያነሣሡ ከሚችሉ ሁኔታዎች ተጠንቀቅ:: ሴቶች በዝሙት ኃጢአት የሚወድቁት የፍቅር ግንኙነት ፍለጋ ሲሆን፣ ወንዶች ግን ብዙውን ጊዜ በሚያዩት ነገር በመነሣሣት በዝሙት ኃጢአት ይወድቃሉ:: ስለዚህ ለዝሙት ከሚያነቃቁ ነገሮች ልትርቅ ይገባል:: ይህ ማለት በቪዲዮ፣ በቴሌቪዥን ወይም በምትታጠቡበት ቦታ፣ ወዘተ . . . ስለምታየው ነገር መጠንቀቅ ማለት ነው::

መ. ከተቃራኒ ጾታ ጋር በአገልግሎትህ ላይ ብዙ ጊዜ አታጥፋ:: የቅርብ ጓደኞችህና አብረሃቸው የምትጸልየው ሁሉ ከአንተ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ሊሆኑ ይገባል:: ባለቤትህም ሁሉን ነገር የምታካፍላት የቅርብ ጓደኛህ እንድትሆን ያላችሁን ግንኙነት ልታሳድጉ ይገባል::

ሠ. ብቻህን ስትሆን፣ በተለይም በጉዞ ላይ ጥንቃቄ አድርግ:: የሚቻል ከሆነ፣ በክርስቶስ የሚያምንና ከአንተ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ካለው ሰው ጋር ሂድ:: ባረፍክበት ሆቴል ብቻህን ሆነህ ሌላ ሴት እንድትቀርብህ አትፍቀድ:: በሆቴል ውስጥ ለሴላ ሴት የምትመሰክርበት ጊዜ አይደለም:: ወይም ከእርሷ ጋር በሆቴል ክፍል ውስጥ የምትጸልይበትም ጊዜ አይደለም:: አንተ ፈተናውን ተቋቁመህ ኃጢአት ባትሠራም እንኳን፣ ሴሎች ሰዎች በዝሙት እንደ ወደቃችሁ ሊያስቡ ይችላሉ:: ይህንን ፈተና መቋቋም የሚያስችል ጥንካሬ አለኝ ብለህ አታስብ:: የተነገረን ፈተና ካለበት ቦታ እንድንሸሽ እንጂ እንድንቆይ አይደለም (ዘፍጥ. 39:6-12፤ 1ኛ ቆሮ. 6:18፤ 2ኛ ጢሞ. 2:22)::

ረ. ተቃራኒ ጾታን እንድታማክር ስትጠየቅ፣ ተመሳሳይ ጾታ ያለው ሰው አብሮህ እንዲሠራ ብታደርግ መልካም ነው:: ሴት ወንጌላውያን ሴቶችን፣ ወንዶች ወንጌላውያን ደግሞ ወንዶችን ሊያማክሩ ይገባል:: በተለይ የምናማክራቸው በቀጣይ ነገር ላይ ከሆነ፣ ያቺን ሴት ለመርዳት ተመሳሳይ ጾታ ያለው ሰው እንዲረዳን ማድረግ አስፈላጊ ነው:: አንድን ሴት ለማማከር ረጅም ሰዓታት ስታጠፉ፣ ብዙ ጊዜ አካላዊና ስሜታዊ መቀራረብ ስለሚፈጠር ወደ



ዝሙት ኃጢአት ልትወድቁ ትችላላችሁ:: በምዕራባውያን አገሮች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዝሙት ፈጽመዋል ተብለው የሚከሰሱት ከጸሐፊያቸው ጋር ወይም ከሚያማክሯቸው ሰዎች ጋር ነው:: አንድ መሪ ከአንዲት ሴት ጋር ረጅም ጊዜን ሲያጠፋ፣ ቀስ በቀስ ሳያስቡት ልባቸው እየተሸነፈ ይሄዳል:: ለምክር የሚመጡ ሰዎችን ተመሳሳይ ጾታ ወዳለው አማካሪ መላክ ካልተቻለ፣ ሊያስጠረጥር የማይችል ቦታ ላይ አማክራቸው:: ለምሳሌ፣ የቢሮውን በር ክፈት:: ስትጸልይላትም እንኳን ፈጽሞ አካሷን አትንካ:: አንድ ጊዜ አንድ ወንጌላዊ የጡት ካንሰር ላለባት ሴት ሲጸልይ እጆቹን በጡቶቿ ላይ ጫነ:: ከዚያ የተነሣ በዝሙት ኃጢአት በመከሰሱ ያንን አገልግሎቱን ስመተው በቅቷል::

ሰ. ከሌላ ሴት ጋር ብቻህን ከምትገናኝ በቡድን ተሰባሰቡ:: የመዘምራን ቡድን አባላት ሁሉ አንድ ላይ ከሆኑ በዝሙት ኃጢአት ሲወድቁ የሚችሉበት ዕድል ይጠብባል:: ነገር ግን ሁለት ወንድና ሴት የመዘምራን ቡድን አባላት ብቻቸውን ሲገናኙ ፈተናው ይመጣል:: በስሜት ስለሚቀራረቡ ፈጥነው በኃጢአት ይወድቃሉ::

ሸ. የድብርት ስሜት ሲጫጫንህ ተጠንቀቅ:: ጥናቶች እንዳመለከቱት ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኃጢአት የሚወድቁት ተስፋ ሲቆርጡ ነው:: ከሚስታቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ሲበላሽ፣ በሥራቸው ቦታ ያሉ ነገሮች ሳይስተካከሉ ሲቀሩ፣ ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ ሳይሆን ሲቀር፣ አገልግሎቸው እንደ ፈለጉት ካለመሄዱ የተነሣ ነው ሰይጣን በዝሙት ኃጢአት ሲጥላቸው የሚሞከረው:: ሰይጣን ብዙ ጊዜ ተስፋ መቁረጣችንን እንድናማክራቸው የሚያመጣልን ተቃራኒ ጾታዎችን ነው:: ያቺ ሴት ስታዝንልንና የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሆንነው ከእኛ ጋር ስትጸልይ፣ በመካከላችን ስሜታዊ መተሳሰር ስለሚያድር ወደ ዝሙት ኃጢአት ልናመራ እንችላለን::

ቀ. በአገልግሎትህ ስኬታማ ስትሆንና ሕልምህ እውን ሲሆን ተጠንቀቅ:: ይህም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስአደጋ

የሚጋለጡበት ሌላ ጊዜ ነው:: ዳዊት ከሳኦል ሲሸሽ በኃጢአት አልወደቀም፣ ነገር ግን ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ጠላቶቹን ካሸነፈና የይሁዳ ንጉሥ ሆኖ ስኬታማና ጠንካራ በነበረበት ጊዜ ነው የወደቀው:: ስኬታማ ስንሆን፣ ራሳችንን ከኃጢአት መጠበቁን እንቀንሳለን:: ለእንደዚያ ዓይነት ፈተናዎች እንዳልተጋለጥን እናስባለን:: በእግዚአብሔር ሳይሆን በራሳችን ጥንካሬ መመካት እንጀምራለን:: ድንገት በኃጢአት እንወድቅና አገልግሎታችን ይበላሻል::

በኃጢአት፣ በተለይም በዝሙት ኃጢአት መውደቅ እንዴት ቀላል ነው! ደስታውና እርካታው ይስበናል:: «ለመጸለይ ብቻ ነው አብረን የምንሆነው:: ንጹሕ የቅርብ ጓደኝነት እንጂ ሌላ ነገር እኮ በመሐከላችን የለም» እንላለን:: በኃጢአት ከወደቅን በኋላም ሰይጣን ሰው ሊደርስብን አይችልም ብለን እንድናስብ ያደርገናል:: «ማንም ሊያውቅ አይችልም:: ለዛሬ ብቻ ነው የማደርገው፣ ሁለተኛ አልደግመውም» ብለን እናስባለን:: ነገር ግን አንድ ቀን እውነቱ ይገለጣል:: ያ ከሆነ በኋላም ደግሞ ከባለቤትህ ጋር ያለህ ግንኙነት ፈጽሞ እንደ በፊቱ አይሆንም:: አንተን ለማመን በጣም ትቸገራለች:: ልጆችህ ለአንተ ያላቸው ክብር ይጠፋል:: (ማስታወሻ፡- ምናልባትም የዳዊት ልጆች ኃጢአት ለመሥራት፣ ለመግደልና ለማመፅ የቻሉት አባታቸው በዝሙት ሲወድቅና ሲገድል ለላዩ ይሆናል::) እግዚአብሔር የሰጠህን አገልግሎት ታጣለህ:: አንድ ጊዜ የጠፋውን ዝናህን ዳግም መመለስ ሲበዛ ያስቸግርሃል:: ያላመኑ ሰዎች ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን እንዲሰድቡ ታደርጋለህ::

በኃጢአት ከመውደቅህ በፊት እነዚህን መራር የሆኑ መዘዞች አስታውስ:: ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር የሠራው ኃጢአት በቤተሰቡ ውስጥ እንደዚህ ያለ ችግር እንደሚያመጣ ቢያውቅ የሚያደርገው ይመስልሃል? የሚያደርገው አይመስልም:: ሰይጣን የድርጊታችን መዘዝ ላይ ሳይሆን በጊዜያዊ እርካታና ደስታው ላይ እንድናተኩር



ያደርገናል:: ከሌላ ሰው ጋር ዝሙት ማድረግ ጀምረሃል? አሁኑኑ አቁመው! በኃጢአት ለመውደቅ ተቃርበሃል? ከዚያ ግንኙነት ራቅ! ሰብቻችሁ ሆናችሁ ዳግም አትገናኙ:: ፈተናውን ልትወጣው አትችልም:: በዝሙት ስንፈተን፣ እንድንጸልይበትና መንፈስ ቅዱስ የምንቋቋምበትን ኃይል እንዲሰጠን እንድንጠይቀው አልተነገረንም:: ከእንደዚያ ያለ ሁኔታ «እንድንሸሽ» ነው የተነገረን (2ኛ ጢሞ. 2:22):: ሮጠህ አምልጥ- እንደ ዮሴፍ በሥጋ መሮጥ ባይሆንም እንኳን፣ ኃጢአት ልትሠራ ከምትችልባቸው አጋጣሚዎች ራስህን አውጣ:: ከእንደዚያ ያለ ሁኔታ ካልራቅን፣ እንደምንቃጠል ሰሎሞን ያስጠነቅቀናል! (ምሳሌ 6:23-29)

28ኛ ጥያቄ:- ሀ) የምታውቀው የቤተ ክርስቲያን መሪ የዝሙት ኃጢአትን ስለ ሠራበት ሁኔታ ግለጽ:: ምንድን ነው ወደ ፈተቀራረቡና ወደ ኃጢአቱ ያመጣቸው? የቤተ ክርስቲያን መሪው ራሱን በኃጢአት ከመውደቅ እንዴት ሊጠብቅ ይችል ነበር? ለ) ኃጢአቱ በሚስቱ፣ በልጆቹ፣ በአገልግሎቱና ከማኅበረሰቡ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ምን ዓይነት ውጤት ያመጣል? ሐ) ሕይወትህንና አገልግሎትህን ፈትን:: በዝሙት ኃጢአት ወይም የዝሙት ኃጢአት በመሥራት ልትጠረጠርበት የምትችልበት የሕይወትህ ክፍል አለ? ፈተናውን ለመወጣትና መንፈሳዊ ዝናህን ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብህ?

## አራተኛ ቀን:- ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ለማድረግ የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ::

## ሳምንታዊ ስብሰባ

## የውይይት ጥያቄዎች:-

1. ሀ) በዚህ ሳምንት ትምህርት ውስጥ ያጠናናቸውንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በአመለካከታቸውና በሚመሩበት ምክንያት ላይ የሚሠሯቸውን ኃጢአቶች ዘርዝር:: ለ) እነዚህ ኃጢአቶች በቤተ ክርስቲያን መሪውና በቤተ ክርስቲያን ላይ ያመጧቸውን ውጤቶች ዘርዝር:: ሐ) የትኞቹ ኃጢአቶች

ይመስሉሃል በቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ በብዛት የማይታዩት? መ) ከእነዚህ ኃጢአቶች መካከል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በብዛት የሚፈተኑት በየትኞቹ ኃጢአቶች ይመስልሃል? ሠ) ለምንድን ነው በእነዚያ ኃጢአቶች የሚፈተኑት? ረ) መሪዎች ራሳቸውን ለመርዳትና በሚፈተኑበት ኃጢአት ላለመውደቅና ድል ለማድረግ እርስ በርስ ምን ማድረግ አለባቸው?

2. ሀ) ካጠናናቸው ኃጢአቶች መካከል የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት በየትኞቹ ነው የሚወድቁት? ለ) እነዚህ ኃጢአቶች በቤተ ክርስቲያን መሪና በቤተ ክርስቲያን ላይ ያመጧቸውን ውጤቶች ዘርዝር። ሐ) የትኞቹ ኃጢአቶች በቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ጐልተው የማይታዩ ይመስልሃል? መ) በየትኞቹ ኃጢአቶች ይመስልሃል በርካታ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚፈተኑት? ሠ) ለእነዚያ ኃጢአቶች በተለየ ሁኔታ የተጋለጡት ለምን ይመስልሃል? ረ) መሪዎች ብዙ ጊዜ የሚፈጽሙትን ኃጢአት ለማሸነፍ ለራሳቸው ወይም እርስ በርስ ምን ማድረግ አለባቸው?

3. ሀ) በዓለማዊ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ትዕቢት የሚገለጥባቸውን መንገዶች በዝርዝር ግለጽ። ለ) በቤተ ክርስቲያን መሪ ልብ ውስጥ ምን ያህል ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ኃጢአት እንዳለ ግለጽ። ሐ) እግዚአብሔር የትዕቢት ኃጢአትን የሚጠላው ለምን ይመስልሃል? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትዕቢት በአመራራቸው ላይ እንዳይታይ ምን ዓይነት ለውጥ ማምጣት አለባቸው?

4. ሀ) የገንዘብ አያያዝ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ምን ያህል መሰናከያ እንደ ሆነ ግለጽ። ለ) አንተ ያለህበት ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብን ለማጥፋት እንዳይፈተኑ ምን ዓይነት አሠራር ትጠቀማለች? ሐ) የቤተ ክርስቲያን አባላት እነርሱንና የገንዘብ አጠቃቀማቸውን እንዲያምኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ምን ሊያደርጉ ይገባል? መ) ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መከፈል የለበትም ወይስ አለበት፣ ከተከፈለስ ምን ያህል መከፈል ይኖርበታል በሚለው ላይ አስተያየትህን ስጥ። በየትኛው ትስማማለህ፣ በየትኛውስ አትስማማም? ለምን? ሠ) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በሙሉ ጊዜያቸው እንዲያገለግሉና ገንዘብ ለማግኘት ብዙ ትግል ውስጥ እንዳይገቡ ለማድረግ ምን ያህል መከፈል አለበት በሚለው ላይ ምን አስተያየት ትሰጣለህ?

5. ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያ ሰዎች እርስ በርስ የሚቀናኑባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ የሚቀኑባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? ሐ) ይህንን ሲያደርጉ ስለ እግዚአብሔር የረሱት ምንድን ነው? መ) ቅናት የቤተ ክርስቲያን መሪ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የተቀበሉ ወጣቶችን እንዳይቀበሉ ሲያደርግ እንዴት ነው ያየኸው? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪው ለምን እንደሚያገለግል ይህ ምን ይገልጣል? ረ) እርስ በርስ ላለመቀናናት እርስ በርስ እንዴት መተያየት እንዳለብን ሲመሩ የሚችሉ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ የጸጋ ስጦታዎችና አገልግሎቶች አንዳንድ እውነቶችን ዘርዝር።

# ትምህርት ሰባት

***የመጀመሪያ ቀን፡-*** የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተለየ ሁኔታ የተጋለጡባቸው ኃጢአቶች (ክፍል 5)

***መሪዎች ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚሠሯቸው ኃጢአቶች (ክፍል 2)***

**6. ሌሎችን ይቅር ያለማለት ኃጢአት።**

አቶ ተስፋሁን ለብዙ ዓመታት በታማኝነት በቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊነት አገልግለዋል። ሆኖም፣ አብዛኛዎቹ ወጣቶች

እንዲኖሯቸው የሚፈልጉት ዓይነት የትምህርት ደረጃ የላቸውም። ስለዚህ ወጣቶች ሽማግሌዎቹን ከአቶ ተስፋሁን ጋር የሚሠራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምሩቅ እንዲቀጥሩ ይጠይቃሉ። ሽማግሌዎቹም ተስማሙ። ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጣው አዲሱ ወንጌላዊ/መጋቢ የተሻለ የትምህርት ደረጃ ስላለው፣ ዋናው ወንጌላዊ እርሱ መሆን እንዳለበት አሰበ። ይህንን አሳቡን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲያቀርብ፣ አቶ ተስፋሁን በአገልግሎት ላይ ብዙ የቆዩ ስለሆነ፣ የበላይ መሆን አለባቸው ብለው ጥያቄውን ውድቅ አደረጉበት። አዲሱ ወንጌላዊም የበላይ ለመሆን ለመሥራት ወሰነ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚበዙትን ወጣቶች አሰባሰበ። ወጣቶቹም ወደ ሽማግሌዎቹ ሄደው፣ አዲሱን ወንጌላዊ የበላይ ካላደረጉ ወጣቶች በሙሉ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንደሚለቅቁ ያስፈራራሉ። ከዚያም ወጣቱ ወንጌላዊ ስለ አቶ ተስፋሁን እንዲህ ሲል የውሸት ወሬ አሰፋፋ፣ «አቶ ተስፋሁን እኮ ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ሰርቀው ቤታቸውን ሠርተዋል።» በሚቀጥለው የሽማግሌዎች ስብሰባ፣ ሽማግሌዎች አቶ ተስፋሁንን ከደረጃቸው ዝቅ አድርገው፣ አዲሱን ወንጌላዊ በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ላይ ይሾማሉ። አቶ ተስፋሁንም ልባቸው ተሰበረ። «በእነዚህ ዓመታት ሁሉ በታማኝነት አገለገልኩ። አሁን ግን ይህ አዲስ ሰውዬ ቦታዬን ወሰደው። ዝናዬንም አጠፋ።» ብለው አሰቡ። ከዚህም የተነሣ በጣም ተማረሩ። በዚያ ንዴት፣ በሚስታቸውና በልጆቻቸው ላይ መጮህ ጀመሩ። ከጓደኞቻቸው ጋር በተገናኙ ቁጥር ደግሞ፣ በሽማግሌዎችና በአዲሱ ወንጌላዊ ላይ ያጉረመርማሉ። አገልግሎት አላቋረጡም፣ ነገር ግን በሚችሉት አቅም ሁሉ ትንሽ ለመሥራት ይሞክራሉ። የአገልግሎት ደስታቸውንም አጡ። አቶ ተስፋሁን የአዲሱን ወንጌላዊ አገልግሎት ለማሰናከል የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ። በአቶ ተስፋሁን ልብ ውስጥ ካለው ምሬት የተነሣ ራሳቸው አቶ ተስፋሁን፣ ቤተሰባቸውና መላው ቤተ ክርስቲያን ተጐዱ።



**1ኛ ጥያቄ፡-** ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከደረሰባቸው ነገር የተነሣ እንዴት በምሬት ሲሞሉ እንዳየህ ግለጽ። ምንድን ነው ያደረጉት? እነርሱንና ሌሎችን እንዴት ነው የነካው? ለ) ማቴ. 6፡12፣ 14-15 ን አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች እኛ ለሰው በምናደርገው ይቅርታና እግዚአብሔር ለእኛ በሚያደርገው ይቅርታ መካከል ስላለው ግንኙነት ምን ያስተምራሉ?

በየእሑዱ፣ በርካታ ክርስቲያኖች በችኩላ፣ «. . . እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንንም ይቅር በለን» ብለው ነው በአባታችን ሆይ ጸሎት አምልኮውን የሚያበቁት። ጌታ ካስተማረው ጸሎት ላይ ያንን ማለት ቀላል ነው፣ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ክፉ ያደረጉባቸውን ሰዎች ይቅር ያላሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ አባላት አሉ። እንዲሁም ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ ብሔር ስላደረገባቸው ነገር ይቅር ያላሉ በሺዎች የሚቆጠሩ የሌላ ብሔር አባላት አሉ።

ጌታ ያስተማረውን ጸሎት ስንጸልይ፣ ምን እንደ ጸለይን እንኳ አናስተውልም። በጸሎታችን የጠየቅነው እኛ የበደሉንን ይቅር በማለት ቅድመ-ሁኔታውን ስናሟላ እርሱ ይቅር እንዲለን ነው። ይህ ማለት እኛ ለሌላ ሰው ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆንን፣ በእነርሱ ላይ ቁጣችን ካልበረደና እንዲቀጡ የምንፈልግ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ፊት የሠራነውን ኃጢአት ይቅር እንዳይለን ፈቅደናል ማለት ነው።

ኢየሱስ ስለ ጸሎት ባስተማረው ላይ በግልጽ እንዳስቀመጠው፣ ሌላ ሰውን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ካልሆንን ወይም ሌሎች ብሔሮች በእኛ ላይ የሠሩትን ኃጢአት ይቅር ካላልን፣ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን ልንጠብቅ አይገባም። ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር በማመስገን ካልተሞላን ወንጌልን መረዳትና የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነት ታላቅነት መረዳት እንደማንችል ያውቃል። አንድ ጊዜ ኢየሱስ በመስቀል ስለ ሞተልን እግዚአብሔር በጣም ትልልቅና በርካታ የሆኑትን ኃጢአቶቻችንን ይቅር እንዳለን

ካወቅን፣ በንጽጽር ሰዎች እኛን የበደሉን ነገር በጣም ትንሽ እንደ ሆነ እንረዳለን:: (ማቴ. 18:21-35 አንብብ::) ስለዚህ እግዚአብሔር የበደልነውን እጅግ የሚበልጥ ኃጢአት ሁሉ ይቅር እንዳለን ካወቅን፣ ሰዎች በእኛ ላይ የሠሩትን ትንንሽ በደሎች ይቅር ለማለት ፈቃደኞች እንሆናለን:: እግዚአብሔር እንዴት ይቅር እንዳለን በሚገባ ከተረዳን፣ ሌሎችን ይቅር እንድንል ያደርገናል:: ነገር ግን ሌሎችን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ካልሆንን፣ እኛ ምን ያህል ኃጢአተኞች እንደ ሆንንና እግዚአብሔር ምን ያህል ይቅር እንዳለን እንዳልተረዳን የሚያሳይ ምልክት ነው:: ያ ደግሞ ኃጢአታችንን ከልባችን እንዳልተናዘዝንና ከዚያ የተነሣ እግዚአብሔር ይቅር እንዳላለን የሚያሳይ ምልክት ነው::

> 2ኛ ጥያቄ:- ሀ) በአንድ መጻፊያ ወረቀት ላይ፣ ባለፈው ሳምንት በእግዚአብሔርና በሰዎች ላይ የሠራሃቸውን ኃጢአቶች ጻፍ:: ተግባርህን ብቻ ሳይሆን፣ ጠልቀህ አሳብህንና ዓላማህን ተመልከት:: ለ) በሌላኛው የወረቀቱ ገጽ ደግሞ፣ በዚህ ሳምንት ሰዎች በአንተ ላይ የሠሯቸውን ኃጢአቶች ጻፍ:: ሐ) የትኛው ዝርዝር ይበዛል፣ በእግዚአብሔርና በሌሎች ላይ የሠራኃቸው ኃጢአቶች ናቸው ወይስ ሰዎች በአንተ ላይ የሠራሃቸው ኃጢአቶች? መ) ይህ ዝርዝር እግዚአብሔር ለአንተ የማያልቅ ይቅርታ ስለ ማድረጉ እንዴት እንደሚያስታውስህ ግለጽ:: ሠ) አንተ በእግዚአብሔር ላይ ከሠራኸው ኃጢአት ጋር ሲነጻጸር ሌሎች ሰዎች በአንተ ላይ የፈጸሙት ኃጢአት ምን ያህል ትንሽ እንደ ሆነ እንዴት ነው የሚያስታውስህ? ረ) ያ ሌሎችን በቀላሉ ይቅር ማለት እንድትችል አድርጎህ እንደ ሆነ አብራራ::

የመሪ ባህሪ ከሚፈተንባቸው ታላላቅ ፈተናዎች ውስጥ አንዱ ሰዎች በእኛ ላይ ሲነሡና ክፉ ሲሆኑብን ነው:: ያን ጊዜ «አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ማለት እንችላለን? ወይስ በጣም ተናድደን ልንጎዳቸው እንፈልጋለን? ሌሎች ጉዳት ሲያደርሱብን ለመበቀል መፈለግ ተፈጥሮአዊ ምላሽ ነው:: ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን መለኮታዊ ምላሽ ሲሆን፣ እግዚአብሔር በእውነት ሕይወታችንን እንደ ለወጠው የሚያሳይ



ነው::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ በምሬት ይያዙና ይቅርታ ለማድረግም ፈቃደኛ አይደሉም:: በመሪዎች የሚቀኑና መልካም ዝናቸውን ማጥፋት የሚፈልጉ ሰዎች ሁልጊዜ ይኖራሉ:: ወይም መሪው የሚወስዳቸውን ውሳኔዎች የማይወዱ ሰዎች ወይም መሪው ከሌላ ብሔር ስለሆነ ብቻ በክፉ አመለካከት የሚያዩ ሰዎች ይኖራሉ:: ብዙ ጊዜ ሰዎች በመሪው ላይ ክፉ ክፉ ነገር በማስወራትና ባሕሪውን በማብጠልጠል መልካም ዝናውን ያጠፋሉ:: እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን አመራር በመቃወምና አንታዘዝም በማለት ከመሪዎች ጋር ለመጣላት ሰዎችን በጐናቸው ያሰልፋሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ካልተጠነቀቁ፣ በምሬት ኃጢአት ውስጥ ልንወድቅና በመጥፎ ሁኔታ ሲያስተናግዱን ሰዎችን ይቅር ማለት ሊያቅተን ይችላል:: ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት መልካም ሆኖ እንዲቀርና ምሬት እንዳይሰማን ለማድረግ እኛ መሪዎች ይቅርታ ማድረግን ልንማር ያስፈልጋል::

## ይቅርታን በተመለከተ መሠረታዊ ትምህርቶች

ሀ. ብዙ ጊዜ ሰዎች እንደ ጐዱን አያውቁም:: መሪዎች ከሚገባው በላይ የሚሰማቸው በመሆኑ ሳይሰደቡ እንኳን የተሰደቡ ይመስላቸዋል:: የምናውቀው ሰው ሰላምታ ሳይሰጠን ካለፈ፣ ብዙ ጊዜ «ያ ሰው በእኔ ተቆጥቷል ማለት ነው» እንላለን:: እነርሱን የሚያናድድ ነገር አድርገናል ብለን ባሰብን ቁጥር፣ አእምሮአችን ብዙ ዓይነት ምክንያቶችን መደርደር ይችላል:: ነገር ግን ያ ሰው በጥልቀት እያሰበ ቢሆንስ፣ ወይም ጥሩ እንቅልፍ ሳያገኝ ቀርቶ ቢሆንስ፣ ወይም በውስጡ የተጐዳበት ነገር ቢኖርስ፣ ሰውየው ደህና ሳይሆን ቢቀር፣ ወይም ጨርሶ ሳያየን ቀርቶ ቢሆንስ ብለን ልናስብ ይገባል:: በሌላ ሰው ልብ ውስጥ ምን እንዳለ አናውቅም:: ብዙ ጊዜ የምንሠራው ኃጢአት ሌላ ሰው ከሚያደርገውና ከሚናገረው ጀርባ ክፉ አመለካከት እንዳለው መገመት ነው:: የሰዎችን ልብ

በሥራቸው ማንበብ እንደምንችል እናስባለን:: ነገር ግን ብዙ ጊዜ እንሳሳታለን:: ብዙ ጊዜ ሰዎች የሚናገሩት ወይም የሚያደርጉት ነገር እኛን ለመጉዳት ባይሆንም እንደዚያ ብለን ስለምናስብ እንጎዳለን::

በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ሰዎች እኛን ይጎዳል ብለው ሳያስቡ አንዳንድ ነገር ይናገራሉ:: ለራሳችን ደጋግመን ስለ ቤተሰባችን ወይም ስለ አመራራችን የተናገሩትን እናብሰለስላለን:: እነርሱ ያንን ያሉት ግድ ሳይሰጡትና ሳያስቡት ይሆናል:: ነገር ግን እኛ ስንሰማው በልባችን በጣም እንጎዳለን:: ለተናገሩት ነገር ፊት ለፊት ስናጋፈጣቸው፣ በጣም ግራ ተጋብተው ምን ዓይነት ስሕተት እንደ ሠሩ እንኳን ሳይረዱ ይቀራሉ::

የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆናችን መጠን፣ ሰዎች ያንን ሲሉ የቻሉበትን ምክንያት ላለመገመት ወይም በቀላሉ ቅር ላለመሰኘት አእምሮአችንን ማስለመድ ይገባናል::

> 3ኛ ጥያቄ:- ሀ) በተሳሳተ መንገድ ሌላ ሰው ያደረገው ነገር አንተን ለመጉዳት ሳይሆን ነገር ግን አንተ  እኔን ለመጉዳት ነው ብለህ ያስብክበት ነገር ግን በኋላ ግምትህ ልክ እንዳልነበር የተረዳህበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ይህ ነገር ሰዎች እንደዚህ የሚያደርጉት እኮ ለዚህ ነው ብለን ፈጥነን መፍረድ እንደሌለብን ምን ያስተምረናል? ሐ) አንድ ሰው አንተን ሆን ብሎ ለመጉዳት ሳይሆን እንዲሁ የተናገረው ነገር አንተን በጣም የጎዳበትን ሁኔታ ግለጽ:: መ) ሌሎች ለሚናገሩት ወይም ለሚያደርጉት ነገር ከፍተኛ ትኩረት በለ መስጠት ይህ ምን ያበተምረናል?

ለ. ይቅርታ አላደርግም የሚልና በልቡ ምሬት እንዲያድግ የሚፈቅድ ሰው በመጨረሻ የሚጎዳው ራሱን ነው:: እርሱ ሁለት ጊዜ ይጎዳል:: በመጀመሪያ፣ ያ ሰው ባደረገው ነገር ይጎዳል:: ነገር ግን ይቅርታ እላደርግም ሲልም፣ በድጋሚ ራሱን ይጎዳል:: ይቅርታ አላደርግም የሚለው ሰው በልቡ ተቆጥቶ ይቅር ባለማለቱ ሌላው ሰው የሚጎዳ ይመስለዋል:: ነገር ግን አብዝቶ የሚጎዳው ይቅርታ አላደርግም ብሎ የሚለው ሰው ነው:: በቅርብ ጊዜ ውስጥ



በሌላ ሰው ላይ ተቆጥተህ ቶሎ ይቅርታ ባለማድረግህ የተፈጠረውን ነገር አስብ:: አንደኛ፣ ሌሊቱን በሙሉ ያ ሰው ያደረገህን ነገር ስታስብና እንዴት እንደምትበቀለው ስታስብ እንቅልፍ የሚባል ነገር በዓይንህ ሳይዞር አደርክ:: ሰውየው ግን ስለ አንተ ጨርሶ ባለማለቡ፣ ድብን ያለ እንቅልፍ ተኝቶ አደረ:: ሁለተኛ፣ በአንተ ቁጣ የተነሣ የምትወዳቸው ሰዎች ይጎዳሉ:: ማለዳ ከእንቅልፍህ ስትነሣ ይደክምሃል:: ትዕግሥት የለሽ ስለምትሆን በባለቤትህና በልጆችህ ላይ ትጮኻለህ:: በሥራ ቦታህም፣ ሰዎችን መታገሥ አቃተህ:: ነገር ግን አንተ የተናደድክበትን ሰው የሚጎዳ ቃል አብዛኛውን ጊዜ ስለማትናገር እርሱ ምንም አይጎዳም:: ይልቁንም፣ ከአንተ ቁጣና ምሬት የተነሣ ነገሩ የማይመለከታቸው ንጹሕ ሰዎች ናቸው የሚጎዱት:: ሦስተኛ፣ ይቅርታ አላ፡ርግለትም በማለትህ ብትጸና በልብህ ያለው ምሬት ስለ ሕይወት ያለህን ግንዛቤ ሁሉ ይለውጠዋል:: መራር፣ ተጠራጣሪ፣ ቁጡ፣ በሰው ላይ የምትፈርድ፣ ወዘተ. . . ትሆናለህ:: አሉታዊ የሆኑ ባሕሪዎች ስለሚታዩብህ ሰዎች ከአንተ ጋር መሆን አይፈልጉም:: ሥራህና ከሰዎች ጋር ያለህ ግንኙነት ስለሚጎዳ፣ ጓደኞችህንና ምናልባትም ሥራህን ልታጣ ትችላለህ:: አራተኛ፣ በጊዜ ሂደት ጤንነትህ መቃወስ ይጀምራል:: ሳይንቲስቶች ጠላት ያለባቸውና በልባቸው በሌላ ሰው ላይ ምሬት ያለባቸው ሰዎች በልባቸው ምሬት ከሌለባቸው ሰዎች ይልቅ ለበሽታ የተጋለጡ እንደ ሆኑ ደርሰውበታል::

ይቅርታ የማታደርግ ከሆነ፣ ያቅርሃል ምግብም አይፈጭልህም:: የልብ ግፊትህ ስለሚጨምር ልብህ ይጎዳል:: አንተ ይቅርታ ባለማድረግህ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ሲደርሱብህ፣ አንተን የጎዳህ ሰው ግን በሕይወትህ ውስጥ እንዲህ ያለ ጉዳት እንዳደረሰብህና በልብህም ምን ያህል ጉዳት እንዳለ ሳያውቅ ይኖራል::

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለሰው ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን በሰው ሕይወት ምሬት በማምጣት ከላይ የጠቀስናቸውን ችግሮች ሲያመጣ እንዴት እንዳየህ አብራራ። ለ) አንድን ሰው ይቅር አለማለት ከሚያመጣው ውጤት እንዳየነው፣ ይቅርታ በማድረግ የሚገኙ የግል ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

ሐ. ይቅርታ አላደርግም የሚል ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ይቆጣል። ለደረሰበት ጉዳትና ችግር እግዚአብሔርን መውቀስ ይጀምራል። ይህ ቁጣ በልባችን አለ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት የለንም ማለት ነው። እግዚአብሔር የማይሰማን ስለሚመስለን አንጸልይም። ስለሚደርቅብንና ብዙም ትርጉም ስለ-ማይሰጠን፣ ቃሉን አናነብም። ኢየሱስ እንደተናገረው፣ ሌላ ሰውን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ካልሆንን፣ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሠራናቸውን ብዙ ኃጢአቶች ይቅር አይለንም።

ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይቅርታ አለማድረግ በጥልቀት ይጐዳናል። ሰውየው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ይጐዳል፣ በልባችን ይቅርታ አለማድረግ እስካለ ድረስ ለሠራነው ኃጢአት የእግዚአብሔርን ምሕረት አናገኝም። በምሬት ስለምንሞላ፣ በዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር ሁሉ ያለን ግንኙነት ይጐዳል። ጤንነታችንንም ይጐዳል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለማደስና መልካም ግንኙነት እንዲኖረንና ጤናችን እንዲጠበቅ ለማድረግ በጣም አስፈላጊው ነገር ይቅርታ ማድረግ ነው።

5ኛ ጥያቄ፡- ከልብህ ይቅር ያላልከው ሰው አለ? ይህንን እንዲገልጥልህ መንፈስ ቅዱስን ጠይቀው። አሁኑኑ ቆም ብለህ የልብህን ቁጣ ማሸነፍ እንድትችልና እያጠፋህ ያለውን ምሬት ማሸነፍ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጠይቀው። (ዕብ. 12፡15ን አንብብ።) በውስጥህ በሚመጣው መፈታት፣ በሚመለሰው ደስታ እና በልብህ በሚመጣው ሰላም ትገረማለህ።

መ. ይቅርታ ማድረግ ምንድን ነው? ይቅርታ፣ ሁለት ሰዎች ሰላም ለመፍጠርና በስምምነት ለመኖር እንደሚፈጥሩት እርቅ ሳይሆን፣ አንድ ሰው ብቻውን ሊያደርገው የሚችለው ነገር ነው።



ይቅርታ ማለት አንድ ሰው መጥፎ ነገር አድርጎብናል ብለን ስናስብና ያንን ሰው ላለመበቀል ወይም ስለዚያ ሰው ክፉ አሳብን በልባችን ላለማስተናገድ ስንወስን ነው። ያ ጉዳት ምናልባት ያ ሰው እኛን ለመጉዳት ሆን ብሎ ያደረገው ውሸት ወይም ስርቆት ሊሆን ይችላል። ወይም ያ ሰው እኛን ለመጉዳት ሳያደርግ አይቀርም ብለን አስበን ሊሆን ይችላል፣ ለምሳሌ፣ ሰውየው በሆነ ነገር ሲስቅ የሳቀው በእኔ ላይ ነው ብሎ በማሰብ ሊሆን ይችላል፣ ምናልባት ግን ሰውየው የሳቀው ጓደኛው በነገረው ቀልድ ሊሆን ይችላል።

ይቅርታ ማድረግ ማለት ያንን ሰው በምንም ዓይነት መንገድ ላለመበቀል የግል ምርጫ መውሰድ ነው። ሰውየውን ለጓደኞቻችን እርሱ ያደረገውን ነገር እንናገርም ማለት ነው። በልባችን በእግዚአብሔር ፊት ሰውየው ባደረገልን ነገር የተጐዳነውን ነገር ለመቻልና ሰውየውን በምላሽ ለመጉዳት አለመፈለግ ነው። እርሱ ብቻውን የሰዎችን ልብ ወደሚያውቀውና የፈለገውን ነገር ማድረግ ወደሚችለው ጻድቅ ፈራጅ ወደ እግዚአብሔር ነገሩን ማቅረብ ነው። በልባችንም ሰውየው ምንም እንዳላደረገን እናስተናግደዋለን።

ሠ. አንድን ሰውን ይቅር አለማለታችንን እንዴት ነው የምናውቀው? አንድን ሰው ከልባችን ይቅር ሳንለው ይቅር ያልነው ሊመስለን ይችላል። በልባችን «እግዚአብሔር ሆይ፣ እርሱን ይቅር ብዬዋለሁ፣ ነገር ግን ፈጽሞ ደግሜ ላየው አልፈልግም። በእኔ ላይ ስላደረገው ነገር ብትቀጣው ደስ ይለኛል።» እንላለን። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ይቅርታ አይለውም። በልባችን የቀረ ጉዳት ካለና እነርሱን በቤተ ክርስቲያን ወይም በሥራ ቦታ ስናገኛቸው ወይም ልናናግራቸው ካልፈለግን ይቅርታ አላደረግንላቸውም ማለት ነው። አስቸጋሪ ጉዳት ሲደርስባቸው በልባችን ደስ የምንሰኝ ከሆነ (ለምሳሌ፣ ላም ሲሞትባቸው፣ የሚወድዱት ሰው ሲሞትባቸው ወይም በሐሰት ሲከሰሱ ደስ የሚለን ከሆነ) ከልባችን ይቅር አላልናቸውም ማለት ነው።

**መጽሐፍ ቅዱስ ይቅርታ ስለ ማድረግ የሚያስተምረን፡፡**

| |
|---|
| ፍ ጥያቄ፡- ማቴ. 18፡21-35ን አንብብ ሀ) በዚህ ታሪክ ውስጥ ጌታው ማንን ይወክላል? ለ) የመጀመሪያው አገልጋይ ማንን ይወክላል? ሐ) ሁለተኛው አገልጋይ ማንን ይወክላል? መ) የዚህ ምሳሌ ዋነኛ ትምህርት ምንድን ነው? |

ሀ. ይቅርታ ማድረግ ምርጫ ሳይሆን ትእዛዝ ነው (ኤፌ. 4፡32፤ ቆላ. 3፡13)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉን ይቅር እንድንል ያዝዘናል፡፡ ከፈለግን የቱን የቱን ይቅር እንደምንል፣ ወይም ሰውየው ይቅርታ ሊጠይቀን ወይም፣ ሰውየው መንገዱን ከቀየረ፣ ወይም ካሳ ከከፈለን ይቅር እንድንለው አይነግረንም፡፡ ይልቁንም፣ ይቅር የማለት ኃላፊነት የተጣለብን በጐዳን ሰውዬ ላይ ምንም ቅድመ - ሁኔታ ሳናስቀምጥ ነው፡፡ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የእኛ ይቅርታ ማድረግ ክርስቶስ የእኛን ኃጢአት ይቅር ካለበት መንገድ ጋር እንዴት እንደሚያያዝ አስተውል፡፡ በእግዚአብሔር ብዙ ኃጢአት እንደ ተሻረላቸው ሰዎች፣ እኛም ሰዎች በግምትም ሆነ በተጨባጭ ላደረሱብን ጉዳት ፈጥነን ይልቅ ልንላቸው ይገባል፡፡ በማቴ. 18፡21-35 ላይ ኢየሱስ ይቅርታን እንዴት መረዳት እንዳለብን ለማሳየት ይቅርታ አላደርግም ስላለ አንድ ባሪያ ምሳሌ ተናገረ፡፡ እኛ እንደ ባሪያው ስንሆን፣ ጌታው ደግሞ የሚወክለው እግዚአብሔርን ነው፣ ሊከፈል የማይችለው ግዙፍ ዕዳ ደግሞ (ኃጢአታችንን ነው የሚያመለክተው)፡፡ የጐዳን ሰውዬ ደግሞ ትንሽ ገንዘብ አበድረነው ያልመለሰልንና ይቅርታ ያላደረግንለት ሰው ነው፡፡ ወይም እግዚአብሔር የመጀመሪያው ባሪያ ያበደረው ትንሽ ዕዳ (ኃጢአት) ባለመሰረዙ ጌታው (እግዚአብሔር) እንዴት እንደ ተናደደ አስተውል፡፡ የጐዳንን ሰው ይቅር አንልም ስንል፣ እግዚአብሔር በእኛ ይቆጣል፡፡

ለ. እግዚአብሔር እኛን ይቅር ለማለት ያለውን ፈቃደኝነት እኛ ሌሎች ሰዎችን ይቅር ለማለት ካለን ፈቃደኝነት ጋር በቅርበት አገናኝቶታል (ማቴ. 6፡12-15ን ተመልከት)፡፡ የሠራናቸውን



ኃጢአቶች ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር እንዳለን እርግጠኛ መሆን የምንችለው ሌሎች ሰዎች በእኛ ላይ የሠሩትን ኃጢአት፣ ወይም በእኛ ላይ ሳይሠሩ አይቀሩም ብለን የምናስባቸውን ኃጢአቶች ይቅር ስንላቸው ነው፡፡

ሐ. እግዚአብሔር ሰውየውን ይቅር ከማለት አልፈን እንድንወድደው ይጠብቃል፡፡ (ማቴ. 5፡43-48ን አንብቡ፡፡) ከእኛ ጋር ጥሩ ግንኙነት በሌላቸው ወይም በጐዱን ሰዎች ላይ የተለየ ባሕሪ እንዲኖረን አልተነገረንም፡፡ ይልቁንም፣ ልንወዳቸውና ልንጸልይላቸው ይገባል፡፡ ለእነርሱ ያለንን ፍቅር የምናሳየው ለእነርሱ በመጸለይ ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዲፈርድባቸው አንጸልይም፡፡ ይልቁንም፣ እግዚአብሔር በእውነት በረከት እንዲባርካቸው ነው የምንጸልየው፡፡ ሌሎች መባረክ ከፈለጉ ንስሐ መግባትና ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው፡፡ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ምን ዓይነት ኃጢአት እየሠሩ እንደ ሆነ እንዲያሳያቸው ልንጸልይ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በልባቸው የሚሠራውን ሥራ እንዲቀጥልና በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ይረዳቸዋል፡፡ እግዚአብሔር እነርሱንና ቤተሰባቸውን እንዲባርክ በየዕለቱ እንጸልያለን፡፡

ይቅርታ ማድረግ ማለት ሰውየውን ፈጽሞ መጉዳት ያለመፈለግ ነው፡፡ ለመበቀል ያለንን ፍላጐት ማቆም ማለት ነው፡፡ በዚያ ፋንታ፣ ከልባችን እግዚአብሔር እንዲባርካቸው እንፈልጋለን፡፡ በውስጣችን ያለውን ቁጣ ከምናሸንፍባቸው መንገዶች አንዱ ስለዚያ ሰው መጸለይን ቀዳሚ ተግባራችን ማድረግ ነው፡፡ ሁልጊዜ ስንጸልይላቸው፣ እግዚአብሔር እነርሱን፣ ቤተሰባቸውን፣ ቤታቸውን፣ እዝመራቸውን፣ ሥራቸው፣ ወዘተ. . . እንዲባርክ ስንጸልይ፣ ምሬቱና ቁጣው እየጠፋ ይሄዳል፡፡

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡- አንድን ሰው ይቅር ለማለትና ለመውደድ የምትቸገር ከሆነ፣ አሁኑኑ ቆም ብለህ ለዚያ ሰው ወይም ለዚያች ሴት ጸልይ፡፡ እግዚአብሔር በመንፈሳዊና በሥጋዊ ነገሮች እንዲባርከው ጸልይ፡፡ ስትጸልይላቸው፣ በልብህ ያለው ቁጣና ምሬት እንዴት እንደሚጠፋ ልብ በል፡፡ |

መ. ስአንድ ሰው ይቅርታ ስናደርግ፣ ስለዚያ ጉዳይ ለሰዎች መናገር እናቆማለን። ስለ ደረሰብን ነገር ያንን ሰው ማማታችንን ከቀጠልንና ያንን ሰው ባየነው ቁጥር ነገሩን ካነሣነው፣ ያንን ሰው ይቅር አላልነውም ማለት ነው። ለሌሎች ሰዎች ለውየው ያደረገንን ስንናገር፣ ብዙ ጊዜ የሰውየውን ስም በማጥፋት ልንጐዳ መፈለጋችን ነው። ፍቅር በደልን እንደማይቆጥር ተነግሮናል (1ኛ ቆሮ. 13:5)። እግዚአብሔር ምሳሌያችን ነው። ኃጢአታችንን ይቅር ሲለን፣ ፈጽሞ ዳግም አያነሣቸውም። ፈጽሞ ያስወግዳቸዋል (መዝ. 103:12ን አንብቡ።)

ሠ. ይቅርታ ማድረግ የእግዚአብሔርን ሥራ (ድርሻ) ለመሥራት እንዳንሞክርና እግዚአብሔር ሁኔታውን እንዲቆጣጠር እንድንፈቅድ ያደርገናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብቻ ዳኛ እንደ ሆነ ይነግረናል። በቀል የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ አይደለም። (ሮሜ 12:17-19ን ተመልከት።) አንድን ሰው ይቅር ስንል፣ ለእግዚአብሔር እጅ አሳልፈን እንሰጣቸዋለን። አንድን ሰው ይቅር ስንል፣ ጻድቅ ፈራጅ ለሆነው እግዚአብሔር ጉዳዩን አሳልፈን ሰጥተናል ማለት ነው። እርሱ ብቻ ሰውየውን እንደ ፈለገ የማድረግ መብት አለው። እግዚአብሔር፣ ቤተ ክርስቲያንን ያሳደዱትን የደርግ ባለ ሥልጣናት እንደ ቀጣ፣ ፈጥኖ ሊቀጣቸው ይችላል። ወይም በመጨረሻ ወደ ገሃነም እስኪጥላቸው ድረስ ቅጣቱን ሊያዘገይ ወይም በእኛ ላይ ላደረጉት ነገር ተጠያቂ ሲያደርጋቸው ይችላል። ወይም ንስሐ ሲገቡ ይቅር ሊላቸውና ልባቸውን ሊለውጥ ይችላል። አንድን ሰው ይቅር እልልም ብለን በቃላችንና በሥራችን ሰውየውን ለመጉዳት ስንሞክር፣ የጉዳዩን መሪ ተቃውመን ስንሠራ የእግዚአብሔርን ድርሻ ለመውሰድ እየሞከርን ነው። ያ ደግሞ ንስሐ ልንገባበት የሚገባን በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ኃጢአት ነው።

ረ. ይቅርታ ማድረግ በሕይወታችን ውስጥ ያደገውን የምሬት ሥር ይነቅላል (ዕብ. 12:15ን ተመልከት።) በአንድ ሰው ላይ ቂም በመያዝ የሚመጣው ምሬት ወይም ይቅርታ ማድረግ ያለመፈለግ ልክ እንደ አረም ነው። በጣም በትንሹ ይጀምርና ሕይወታችንን ሁሉ እስኪቆጣጠረን ድረስ ያድጋል። ይቅርታ ማድረግ ብቻ ነው በሕይወታችን ምሬት እንዳያድግ የሚያቆመው።

ሰ. ይቅርታ ስናደርግ፣ በሕይወታችን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ዳግም ይለቀቃል። በኤፌ. 4:29-32 ላይ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን የምናሳዝንበትና ሥራውን የምንገድብበት ዋነኛ ነገር በሕይወታችን ይቅርታ አለማድረግን በመፍቀድ እንደ ሆነ በግልጽ አሳይቷል። ከሌሎች ጋር በቁጣ የምንነጋገረው፣ የምንሳደበውና ልንበቀላቸው የምንፈልገው፣ በልባችን ውስጥ ምሬትን ስንይዝ ነው። ይህንን ማቆም የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይቅርታ ማድረግ ነው። ይቅርታ ካደረግን በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስ ዳግም በሕይወታችን ለመሥራት ይደሰታል።

## ይቅርታን በተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያዎች

ሀ. ስአንድ ሰው ይቅርታ ስናደርግ፣ የተፈጠረው ነገር ኃጢአት አይደለም ማለታችን አይደለም። ለሠሩት ኃጢአት፣ ለተሳሳተ አመለካከታቸው ወይም ድርጊታቸው ሰበብ እንደረድርላቸዋለን ማለትም አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲታደስ በእኛ ላይ ለፈጸሙት ኃጢአት ወደ እኛ መጥተው ይቅርታ ሊጠይቁን አይገባም ማለታችንም አይደለም። ይልቁንም፣ ይቅርታ ስናደርግ፣ የሠሩት ነገር በእኛና በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንደ ሆነ ማመናችን ነው። ለእነርሱ ምንም ዓይነት ሰበብ እንደረድርላቸውም ወይም ያደረጉትን ነገር ልንደብቅላቸው አያስፈልግም።

(ማስታወሻ፡- በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔርን ወይም ሰዎችን ይቅርታ ስንጠይቅ፣ ለድርጊታችን ሰበብ ልንደረድር አይገባም። ኃጢአታችንን መቀበል አለብን። ሰበቦችን መደርደር ማለት ኀላፊነታችንን አልተቀበልንም ማለት ነው። ይልቁንም

ጥፋታችንን በሌላ ሰው ላይ ወይም ሁኔታ ላይ ለማላከክ እየሞከርን ነው። ጥፋታችንን በሌላ ሰው ላይ እስካላከክን ድረስ፣ ኃጢአት እንደ ሠራን አላመንንም ማለት ነው። ስለዚህ ኃጢአታችንን ባለመናዘዛችን ይቅርታ ልንቀበል አንችልም።)

ኢየሱስ ለሰዎች ይቅርታ ሲያደርግ፣ የሠሩት ነገር ስሕተት እንዳልሆነ አልነገራቸውም። በእነርሱ ፈንታ ሆኖ ሰበብ አልደረደረላቸውም። እነርሱ የሠሩት ኃጢአት እንደ ነበረ ግን እውቅና ሰጥቷል። ይቅርታ ካደረገላቸው በኋላ፣ የኃጢአት ሕይወታቸውን እንዲተዉ ይነግራቸዋል (ዮሐንስ 8:11)። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲፈወስ ኃጢአት መሥራትን መተው አለባቸው። ኢየሱስ የሰቀሉትን ሰዎች ቅር እንዲልለት ወደ እግዚአብሔር አብ ሲጸልይ፣ ሰዎቹ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማደስ ምንም ማድረግ የለባቸውም ማለቱ አልነበረም። ከእርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲስተካከል፣ ኃጢአታቸውን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ፣ ይቅርታን ለመጠየቅና እምነታቸውን በኢየሱስ ላይ ለማድረግ ኃላፊነት ነበረባቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እኛ ይቅርታ ስናደርግ በእኛ ላይ ጥፋት የሠሩት ወይም የጐዱን ሰዎች በእኛ ላይ ለሠሩት ጥፋት አያገባቸውም ማለታችን አይደለም። እነርሱ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመቀበል፣ ኃጢአታቸውን መናዘዝና ድርጊታቸውን መቀየር አለባቸው። ለሰዎች ይቅርታ ስናደርግ፣ ሌሎች በእኛ ላይ ከሠሩት ጥፋት የተነሣ የተጐዳውን ልባችንን እንጠግናለን፣ እንዲሁም ለሁኔታው የምንሰጠውን ምላሽም እናስተካክላለን።

ለ. ይቅርታ ስናደርግ፣ በቅድሚያ የምንጠግነው ራሳችንን እንጂ ሌሎችን አይደለም። ይቅርታ ለማድረግና ይቅርታ ለመጠየቅ እግዚአብሔር በሌላ ሰው ድርጊትና ፈቃደኝነት በኃላፊነት አይጠይቀንም። የጐዱን ሰዎች በእኛና በእግዚአብሔር ላይ ለሠሩት ኃጢአት በሕይወታቸው ላይ ኃላፊነት ይወስዳሉ። ከእርሱ ጋር



ያላቸው ግንኙነት እንዲታደስ፣ ንስሐ የመግባትና ይቅርታ የመጠየቅ ኃላፊነት አለባቸው። ነገር ግን እኛም ሰዎች ሲጐዱንና ሲያስቀይሙን እነርሱን በተመለከተ ስላለን አመለካከትም ሆነ ስለ ድርጊታቸው ተጠያቂ ነን። ይቅርታ ስናደርግ፣ አመለካከታችንን በተመለከተ ኃላፊነት ወሰድን ማለት ነው። በእኛ ልብ ውስጥ ያለውን ጉዳትና ሕመም ለመልቀቅ መርጠናል ማለት ነው። ጉዳት ያደረገብንን ሰው በምላሹ ሳንጐዳ፣ የራሳችንን ጉዳት እናስታምማለን ማለታችን ነው። (በትንሹ ይህ ነገር እግዚአብሔር እኛን እንዳይጐዳንና የዘላለም ሞት እንዳይፈርድብን ሲል ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከተጐዳልን ጋር ይመሳሰላል።) ይቅርታ ስናደርግ፣ ያለንን ቂጣ ሁሉ፣ ጥላቻችን ወይም በተፈጥሮአችን የሚመጣውን የመበቀል ፍላጐት ሁሉ እናስወግዳለን ማለት ነው። ይልቁንም፣ እግዚአብሔር እንዲባርካቸው እንፈልጋለን።

ሐ. ለሌላ ሰው ይቅርታ ስናደርግ፣ ለሠሩት ስሕተት ስርየት መስጠታችን አይደለም። እግዚአብሔር ብቻ ነው የኃጢአት ስርየት የሚሰጠው። ስርየት ማግኘት ማለት ለሠሩት ኃጢአት ከሚደርስባቸው የእግዚአብሔር ፍርድ ነፃ ማድረግ (መፍታት) ነው። ሰዎች ለሠሩት ኃጢአት እግዚአብሔር ተጠያቂ እንደማያደርጋቸው ልንነግራቸው አንችልም። ልክ እንደዚያው ለሠሩት ነገር እግዚአብሔር ተጠያቂ እንደማያደርጋቸውም ልንነግራቸው አንችልም። ይልቁንም፣ የምንነግራቸው በእነርሱ ቂም እንደማንይዝ ወይም ያደረጉን ነገር በእኛና በእነርሱ መካከል ያለውን ግንኙነት እንደማይነካ ነው። እነርሱን ለመበቀል ያለንን ፍላጐት በመተው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲታደስና ከዚያም የተነሣ የእርሱን ይቅርታና በረከት እንዲያገኙ ነው የምንፈልገው።

መ. ለአንድ ሰው ይቅርታ ስናደርግ፣ ከሰውየው ጋር «እርቅ» አይደለም የፈጠርነው። መታረቅ ማለት ሁለቱም ወገኖች ይቅርታ ተደራርገው ያላቸውን ግንኙነት ሲያድሱ ነው። ለሌላ ሰው ይቅርታ

ስናደርግ ፍላጐታችን ያ ነው:: ነገር ግን ሌላ ሰው የእኛን ይቅርታ እንዲቀበል ልናስገድደው አንችልም:: ያ የእነርሱ ምርጫ ነው:: ለዚያ ነው ጳውሎስ ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ያለው (ሮሜ 12:18):: በመስቀል ላይ በመሞት ኢየሱስ ሰዎች ሁሉ እርቅና የኃጢአት ስርየት እንዲያገኙ አስችሏል:: እግዚአብሔር የራሱን ድርሻ ተወጥቷል:: የጠፉ ልጆቹን ለመቀበል እጆቹ ሁልጊዜ የተዘረጉ ናቸው (ሉቃስ 15:11-24):: ወደ እኛ እንዲመጣና ከእኛ ጋር ኅብረት ለማድረግ ሲል የልባችንን በር እስክንከፍትለት ድረስ በውጪ ቆሞ ያንኳኳል (ራእይ 3:20):: ነገር ግን ሰዎች ልባቸውን ሲከፍቱ ብቻ ነው እርቅ የሚፈጠረው:: ሰዎች ንስሐ እስካልገቡና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔርን ይቅርታ እስካልተቀበሉ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አይችሉም:: አማኝ እንደ መሆናችን መጠን፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያድሱ የምንለምን «የእርቅ» ስባኪዎች ነን (2ኛ ቆሮ. 5:16-21):: በተመሳሳይ መንገድ የጐዱን ሰዎች መጥተው ይቅርታ እስካልጠየቁን ድረስ ከእነርሱ ጋር መታረቅ ግንኙነታችንን ማደስ አንችልም::

ሠ. ይቅርታ ስናደርግ፣ ሰውየው ያደረገንን ነገር እንረሳዋለን ማለት አይደለም:: ብዙ ጊዜ ሰው ያደረገንን ነገር በተመሰይ ነገሩ በጣም ከጐዳን መርሳት ያቅተናል:: ይልቁንም፣ ያንን ጉዳይ ደግሞ ላለማንሣት ቃል የምንገባበት ምርጫ ነው:: በእኛ ላይ የሠሩትን ኃጢአት እንመዘግብም (1ኛ ቆሮ. 13:5):: ላደረጉብን ነገር ፈጽሞ ልንጐዳቸው አንፈልግም:: ከእነርሱ ጋር ስንሆን በእኛ ላይ ምንም ነገር እንዳላደረጉ ነው የምንሆነው:: ይቅርታ ሳናደርግ ስንቀር፣ ብዙ ጊዜ በአእምሮአችን ሰውየው ያደረገንን ነገር እንመዘግባለን:: ይቅርታ ስናደርግ፣ ሰዎች የሠሯቸውን ስሕተት የጻፍንበትን ወረቀት እንደ መቅደድ ነው:: ሰውየው ስላደረገብን ነገር እርሱን መውቀሳችንን እናቆማለን::

ረ. ለአንድ ሰው ይቅርታ ስናደርግ፣ ለሚከተሉት ነገሮች



ራሳችንን እናስገዛለን:-

1) ሰውየውን በምንም ዓይነት መንገድ መበቀልን እንተዋለን:: ሰውየው በምንም ዓይነት እንዲጐዳ እንፈልግም:: ይልቁንም፣ እንደ ፈለገ እንዲያደርጋቸው ለእግዚአብሔር እጅ አሳልፈን እንሰጣቸዋለን::

2) ሰውየው በእኛ ላይ ያደረገውን ስሌላ ሰው መንገር እንተዋለን:: ስሌላ ሰው መናገር ማለት ሰውየውን ለመጉዳት የምንሞክርበት መንገድ ነው:: በሌሎች ሰዎች ዓይን ዝናቸውን የምናጠፋበት መንገድ ነው:: ይህ የሐሜትና የበቀል ኃጢአት ነው:: እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ስለ ሠራነው ኃጢአት ለሌሎች ሰዎች አይናገርም:: ስለዚህ ስለ ጐዱን ሰዎች ለሌላ ሰው መንገር አይገባንም::

3) ይቅርታ ማድረግ ማለት «ከፍርድ» ይልቅ «ምሕረት» መፈለግ ማለት ነው:: ፍትሕ ማለት ለሰዎች የሚገባቸውን መስጠት ነው:: ምሕረት ማለት ደግሞ ሰዎች ቅጣት ቢገባቸውም አለመቅጣት ማለት ነው:: እግዚአብሔር አይፈርድብንም:: ያንን ቢያደርግ፣ ለኃጢአታችን ይቅርታን ሳይሆን ቅጣትን ነበር የሚሰጠን:: ይልቁንም እግዚአብሔር በምሕረቱና በጸጋው ነው የሚገናኘን:: የማይገባንን የይቅርታና የደኅንነት ስጦታ ሰጠን:: በእኛ ላይ በጽድቅ የሚፈርደው ምሕረቱንና ጸጋውን ሳንቀበል ስንቀር ነው::

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንድን ሰው ይቅር ስንል፣ ፍላጐታችን ሰውየው እንዲፈረድበት አይደለም:: ይልቁንም፣ ጸጋና ምሕረትን ለማሳየት መፈለጋችን ነው:: የእኛ ፍላጐት እርቅ ነው:: እኛ የምንፈልገው እግዚአብሔር ያንን ሰው ይቅር እንዲለውና እንዲባርከው ነው፣ ያ ማለት ኃጢአተኝነታቸውን ሲረዱና የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል ማለት ነው:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎቹ ኃጢአትን እየሠሩ እንደ ሆኑ እንዲያውቁ ስንል ፊት ለፊት እንጋፈጣቸዋለን፣ ያንን የምናደርገው ግን ለራሳችን ጥቅም

ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም ነው። ነገር ግን ለሰዎቹ ይህንን ስንነግራቸው፣ እነርሱን ለመጉዳት፣ ለማሳፈር ወይም ለማስቆጣት ሳይሆን፣ ረጋ ብለን በጨዋነት ልንነግራቸው ይገባል።

(ማስታወሻ፦ መቼ ነው ወደ ሰዎቹ ሄደን ሳደረጉት ነገር ፊት ለፊት የምንጋፈጣቸውና በልባችን ያለውን ጉዳት የምናከመው? ይሄ ለመመለስ በጣም የሚከብድና የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚጠይቅ ነገር ነው። ሰውየው አንተን እንደ ጐዳህ የማያውቅ ከሆነ፣ ወደ እርሱ ሄደህ ስላደረገው ነገር ፊት ለፊት መጋፈጥና ይቅርታ ማድረግ አያስፈልግህም። ይልቁንም፣ የራስህን አስተሳሰብ አስተካክለህ ይቅርታ አድርግለት። ነገር ግን አንድ ሰው እያወቀ ከጐዳህ ወደዚያ ሰው ሄደህ ይቅርታ ልታደርግለት ይገባል። የዚህ ዓላማ ሰውየውን መክሰስ ሳይሆን፣ እርቅ መፍጠር ነው። ወይም ሰውየው የሚያደርገው ነገር ሌሎችን የሚጐዳና ለመንፈሳዊ ዕድገታቸውም አደገኛ ከሆነ፣ እንዲያድግና የሠራውን ስሕተት እንዲረዳ ለማድረግ በመፈለግ ፊት ለፊት ልትጋፈጠው ይገባል። ነገር ግን ይህንን ማድረግ የሚገባህ በልብህ የሚያስፈልግህን ይቅርታ በሙላት ካደረግህ በኋላ ነው።)

ሰ. ይቅርታ ማድረግ ልባችንን ይፈውሳል። ምንም እንኳን ከሰውየው ጋር መታረቅ ብንፈልግም፣ ዋነኛው ትኩረታችን ሌላ ሰውን ይቅር ላለማለት ስንል ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት እንዳይጐዳ ነው። በሌሎች ላይ መራራ በመሆን በሕይወታችን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ማጣት አንፈልግም። ሌላው ትኩረታችን ቁጣና ምሬት በሕይወታችን አድጐ እንዳይቆጣጠረንና ሰውየው ከጐዳን በላይ ራሳችንና የምንወዳቸውን ሰዎች እንዳንጐዳ ነው።

ሸ. ይቅርታ ስናደርግና ቁጣችንን ስንተው፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት እናሳያለን። ብዙ ጊዜ አንድ ሰው እኛን ለመጉዳት የሆነ ነገር ሲያደርግ፣ በእግዚአብሔርም ላይ እንቆጣለን። «እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ሁሉን ነገር የምትቆጣጠር ቢሆን ኖሮ፣ ይህ ነገር እንዳይደርስብኝ ታደርግ ነበር።) ብለን በልባችን



እናበባለን። እናም «ለምንድን ነው እገሌና እገሌን የማትቀጣው? ምን እንዳደረጉብኝ አትመለከትም? ግድ አይልህምን?» ብለን እናጉረመርማለን። በልባችን ምሬት በተሰማን ቁጥር፣ በተዘዋዋሪ በእግዚአብሔርም ላይ ምሬት ይሰማናል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲሆን የፈቀደውን ነገር እምቢ ማለት ስለሆነ ነው። (ማስታወሻ፦ አንዳንድ ጊዜ ልጃችን ሲሞትብን ቁጣችን በእግዚአብሔር ላይ ስለሚሆን በእርሱ ላይ ምሬት ይሰማናል። በእግዚአብሔር ላይ ያንን ቁጣ ልክ የበደለንን ሰው ይቅር እንደምንል ልንተወው ይገባል።) ቁጣችንን ስንተው፣ እግዚአብሔር በሚጐዳ ሁኔታ ውስጥ እውነተኛ ፍትሕን እንደሚያመጣ ያለንን እምነት ነው የምናሳየው። ነገሩ እንዲከሰት እንዴት እንደ ፈቀደ ባልረዳም፣ እግዚአብሔርንና ፍቅሩን እምናስሁ ማለታችን ነው። መራራ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንኳ ሁኔታውን ወደ በረከት እንደሚለውጠው በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት እናሳያለን (ሮሜ 8:28)።

ቀ. ሌሎችን የሚጐዳ ነገር ስናደርግ ራሳችንን ይቅር ማለትን ልንማር ይገባል። ሰዎችን በኃይል የሚጐዳ ነገር የምናደርግበት ጊዜ አለ። ምናልባት ውርጃ በማድረግ የራሳችንን ልጅ ገድለን ይሆናል ወይም ተፋትተናል። ወይም ልጆቻችን እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ባለማድረጋችን ዐመፀኛ ሆነዋል። ወይም በጣም ተቆጥተን ልጃችንን በመምታታችን አካለ ስንኩል ሆኖብናል። እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግልን ከጸለይን በኋላም እንኳን በበደለኝነት ስሜት ተሸንፈናል። ራሳችንንም «ይቅር» ማለት አለብን። ይህንን የምናደርገው የሠራነው ስሕተት መሆኑን በማመን ነው። እግዚአብሔር ይቅር እንዳለንና ንስሐ በገባነው ኃጢአት በኃላፊነት እንደማይዘን እናውቃለን። ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን በእኛ ጥፋት የመጣ መራራ ገጠመኝ ለራሱ ክብር እንዲለውጠው ጉዳዩን ለእግዚአብሔር እንተወዋለን። የበደለኝነት ስሜት ለራሳችን ይቅርታ የምንነፍግበት መንገድ ሲሆን፣ ልክ እንደ ምሬት

ሕይወታችንን በመቆጣጠር መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ በኃይል እንዳይሠራ ያደርጋል፡፡ ለራሳችን ይቅርታ ሳናደርግ ስንቀር፣ ያለማመን ምልክት ነው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ሙሉ በሙሉ እንዳስወገደውና በእነዚያም በኃላፊነት እንደማይጠይቀን የገባውን ቃል አለመቀበል በመሆኑ ነው (መዝ. 103:12፤ ሮሜ 4:7-8)፡፡

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከላይ በይቅርታ ላይ የተሰጠው ትምህርት አብዛኛዎቹ አማኞች ይቅርታን ከሚረዱበት መንገድ ጋር ያለውን ልዩነት አነጻጽር፡፡ ለ) አማኞች እነዚህን እውነታዎች ማወቅ ያለባቸው ለምን ይመስልሃል?

## ሌሎችን ያደረግነውን ይቅርታ ለመጠበቅ መውሰድ ያለብን እርምጃዎች

አንድ ሰው አንተን የሚጐዳ፣ የሚያስቆጣ፣ የሚያማርርና ለበቀል የሚያነሣሣህን ነገር እንዳደረገ ካመንክ፣ ምንድን ነው ማድረግ ያለብህ?

ሀ. የጐዳህን ሰው ስም ለማጥፋት ስትል ጉዳዩን ለማንም ሰው አትናገር፤ ስሌሎች ሰው ያደረገንን ነገር ስንናገር፣ ያንን የምናደርገው አብዛኛውን ጊዜ የሰውየውን ስም ለማጥፋት ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ስለሆነው ነገር ለሌሎች ስንናገር፣ የሠራነው የሐሜት ኃጢአት ነገሩን ያባብሰዋል፡፡ አንድ ጊዜ ጉዳዩ ለሎች ጋ ከደረሰ፣ ሌሎች ሰዎች ስለሚሰሙት፣ በደሉን ያደረሰው ሰው ስሙንና ክብሩን ለመጠበቅ ሲል ይቅርታ መጠየቅ አስቸጋሪ ይሆንበታል፡፡ ውስጣዊ ፈውስና ሰላም ለማግኘት ለቅርብ ጓደኛህ መንገር ካስፈለገህ፣ ጓደኛህ ለማንም እንደማይናገር እርግጠኛ ሁን፡፡ ስትነግረው ግን የሰውየውን ስም በማያጠፋና በልብህ ያለውን ሥቃይ በሚቀንስ መንገድ ይሁን፡፡

ለ. እነርሱ ባሉበት አካባቢ ስትሆን ደስ ለመሰኘት ወስን፡፡ ምናልባት አንተን እንደ ጐዱ ወይም እንዴት ባደረጉት ነገር ልትጐዳ እንደ ቻልክ ላይረዱ ይችላሉ፡፡ በአንተ ሳይ ጥፋት እንደ



ሠሩ ቢያውቁም እንኳን፣ አንተ ባለህበት ምቾት እንዲሰማቸው ይቅርታህን አሳያቸው፡፡ ሰውየው ዳግም የቅርብ ጓደኛ ላይሆን ይችላል፣ ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ እንደዚያ ለማስተናገድ ወስን፡፡

ሐ. የሚቻልህ ከሆነ፣ ለሰውየው ምን እንደ ጐዳህ ንገረው፡፡ ሰውየው ምቾት ካልተሰማው፣ ጨዋ በመሆን ይቅርታህን አሳየው፡፡ ልክ አንተ የበደልከው፣ የጐዳኸው ሰው አንተን በመረዳትና በጨዋነት ሊያስተናግድህ እንደምትፈልግ፣ አንተም እንዲሁ አድርግለት፡፡ ልክ ዮሴፍ የወንድሞቹን ፍርሃት እግዚአብሔር ለበጐ አደረገው ብሎ እንዳበረደ (ዘፍጥ. 45:5፤ 50:15-21)፣ እነርሱን በማይከስ ወይም ይቅርታ ለመጠየቅ በማያስቸግራቸው መንገድ ግለጥላቸው፡፡ የምትፈልገው ላደረሰብህ ጉዳት እርሱን መቅጣት አይደለም፡፡ ይልቁንም፣ ሌሎች ሰዎች ላይ የሚያደርጉትን የሚጐዳ ነገር በማየት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ፈልገህ ነው፡፡

መ. ነገሩ በሁለታችሁ መካከል ምሥጢር እንደ ሆነና ለማንም እንደማትናገር አረጋግጥላቸው፡፡ ብዙ ጊዜ የሰዎቹ ፍርሃት እነርሱን ለማሳፈር ስትል ነገሩን ለሌላ ሰው ትነግርብኛለህ የሚል ስጋት ነው፡፡ ነገሩ በሁለታችሁ መካከል የሚቆይ ምሥጢር መሆኑን በመናገር ያንን ፍርሃት እንዲያሸንፉ እርዳቸው፡፡

ሠ. በቶሎ ይቅርታ ማድረግህን አረጋግጥ፡፡ በቁጣችን መካከል ፀሐይ እንዳይገባ ተነግሮናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ይቅርታ ማድረግ አለመፈለግህን በፍጥነት አስወግድ፡፡ ፈጥነን ይቅርታ ካላደረግን፣ ሰይጣን በሕይወታችን ውስጥ ድርሻ ስለሚያገኝ ምሬትንና ይቅርታ አለማድረግን በእኛ ላይ ያመጣል (ኤፌ. 4:26-27)፡፡ ልክ እንደ ተጐዳህ ይቅርታ አድርግ፡፡ እነዚያን ጉዳቶች ይዞ የመቆየት ስሜት ተቋቋም፡፡ ምክንያቱም በልብህ ውስጥ ምሬት እንዲያድግ የሚያደርግ በመሆኑ ነው፡፡ በውስጣችን ቁጣና ምሬት እንዲያድግ ከመፍቀድ ይልቅ ልክ እንደ ተጐዳን ይቅር ማለት ይቀላል፡፡ በጉዳዩ ሳይ ሐሜትና ቁጣ ከመቀሳቀሱ በፊት ወዲያውኑ እርቅ ለመፍጠር መሞከር ያስፈልጋል፡፡

ረ. ለዚያ ሰው ወዲያውኑ መጸለይ ጀምር:: እግዚአብሔር እንዲቀጣው አትጸልይ፣ ምክንያቱም ያ በልብህ እስካሁን ቁጣ እንዳለ የሚያሳይ በመሆኑ ነው:: ይልቁንም፣ ልክ እንደ ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ጸልይ:: ይህ በረከት በቀዳሚነት የሠሩትን ኃጢአት እንዲመለከቱ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲስተካከልና እግዚአብሔር በልባቸው ለሰምና ፍቅር እንዲያመጣ ነው:: በጸሎት መንፈስ የእግዚአብሔርን እውነተኛ በረከት ተመኝላቸው::

9ኛ ጥያቄ:- ሀ) ክርስቲያኖች ሌሎችን ይቅር ለማለት የሚቸገሩባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝር:: ለ) በሕይወትህ ሌላ ሰው አንተን በጣም የጐዳበትን ሁኔታ ግለጥ:: ሐ) ሰውየውን ይቅር ማለት ለምን እንደሚያስቸግር አብራራ:: መ) በምን ያህል ፍጥነት ሰውየውን ይቅር ማለት ትችላለህ? ረጅም ጊዜ የሚወስድብህ ከሆነ፣ ሰውየውን ፈጥነህ ይቅር ባለማለትህ በሕይወትህ ምን አሉታዊ ነገር ተከሰተ? ሰውየውን እስካሁን ድረስ ይቅር ያላልከው ከሆነ፣ ከዚህ የተነሣ በሕይወትህ የተከሰቱት አሉታዊ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ሠ) ከላይ ያሉትን እውነቶች አስቀድመህ አውቀሃቸው ቢሆን ኖሮ፣ እንዴት ይረዱህ ነበር? በልብህ ነጻነትን ታገኝ ዘንድ ለምን አሁኑኑ እነዚህን ይቅርታ የማድረግ እርምጃዎች አታጠናቸውም:: ረ) አብዛኞዎቹ የእንተ ቤተ ክርስቲያን አባላት ይቅርታ ያላደረጉለት ሰው ያለ ይመስልሃል? የሚመስልህ ከሆነ፣ ይቅርታ ካለማድረግ አመለካከታቸው የተነሣ በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት ላይ ምን እንደሚፈጠር የሚያውቁ ይመስልሃል? ሰ) ይህ በዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተማር ካለብን እጅግ አስፈላጊ ትምህርቶች አንዱ የሆነው ለምን ይመስልሃል? በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታን በተመለከተ እንዴት እንደምታስተምር ዕቅድህን በጽሑፍ አዘጋጅ::

## ላደረግናቸው ነገሮች ይቅርታና ካሳ

ክርስቲያኖች እንዳቸው በአንዳቸው ላይ የሚሠሯቸው ልዩ ልዩ ኃጢአቶች አሉ:: አንዳንድ ኃጢአቶች በሌላ ሰው ላይ



የሚያመጡትን ጉዳት ለመቀነስ ምንም ማድረግ አንችልም:: ለምሳሌ፣ ዝሙት ስንሠራ፣ ኃጢአታችን በባላችን ወይም በሚስታችን ላይ የሚያመጣውን ነገር ምንም ብናደርግ ልንቀይረው አንችልም:: ልናደርገው የምንችለው ነገር በረጅም ጊዜ ሂደት ዳግም እንዲያምኑን መጣር ብቻ ነው:: ነገር ግን እንደ መስረቅና ሐሜት የመሳሰሉትና ያደረስነውን ጥፋት በከፊልም ቢሆን መመለስ የምንችልባቸው ኃጢአቶችም አሉ:: እንደዚያ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ምን እንድናደርግ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን?

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች በይቅርታና በካሳ መካከል ያለውን ግንኙነት በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል:: አንድን ሰው «ይቅርታ» ስንል፣ ያደረስነውን ጉዳት መቀልበስ እንዳለብን የሚያስቡ ክርስቲያኖች አሉ:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ሰው ላይ ጥፋት ስንሠራ፣ ጉዳቱን በጥቂቱም እንኳን ቢሆን መቀልበስ ከቻልን፣ ያንን ጉዳት ለመቀልበስ ከልባችን እንድንጥር ይነግረናል:: ለምሳሌ፣ ከሌላ ሰው ገንዘብ ከሰረቅን ሰውየውን ይቅርታ ስንጠይቀው የሰረቅነውን ገንዘብ ለመመለስ ጥረት ካላደረግን፣ ይቅርታ እንዳልጠየቅነው ይቆጠራል:: በሰውየው ላይ ያደረስነውን የስሜት ጉዳት ልንቀለብሰው አንችልም:: ነገር ግን ገንዘቡን በማጣት ያደረስነውን ጉዳት ማስወገድ እንችላለን::

መጽሐፍ ቅዱስ ከልባችን ይቅርታ ከጠየቅን፣ ሁልጊዜ የሰረቅነውን ገንዘብ መመለስ እንደምንፈልግ ይናገራል:: በዘሌዋውያን 6:1-7 አንድ ሰው የሌላ ሰውን ገንዘብ ቢያጠፋ፣ ለእግዚአብሔር መባን ከመስጠቱ በፊት፣ ከሰውየው የወሰደውን ገንዘብ ከ20% ወለድ ጋር መመለስ እንዳለበት ይናገራል:: ያን ጊዜ ብቻ ነው በእግዚአብሔር ፊት ምሕረት ለማግኘት መሥዋዕት የሚያቀርበው:: ይህ የሚስተምረው በሌላ ሰው ላይ ላደረስነው ጥፋት እውነተኛ ይቅርታ የምንጠይቅ ከሆነ፣ በሰውየው ላይ ያደረስነውን ጉዳት ለመቀልበስ በምንችለው ኃይል ሁሉ መጣር እንዳለብን ነው:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰውን ያማሑ ከሆነና በሐሰት

ስሙን ካጠፋሁ፣ ለሠራሁት የሐሜት ኃጢአት ሰውየውን ይቅርታ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን፣ ሐሜቴን ወደ ሰሙ ሰዎች ሁሉ ሄጄ የተናገርኩት ሁሉ ስሕተት እንደ ሆነ እናገራለሁ ማለት ነው:: የሰውየውን ስም በማጥፋት ያደረስኩትን ጉዳት መጠገን አለብኝ:: ወይም ያ ማለት ከአንድ ሰው ገንዘብ ከሰረቅሁ፣ ያንን ገንዘብ መመለስ አለብኝ ማለት ነው:: ያ ምንም እንኳን እኔ ለጊዜው ብጉዳም ማለት ነው:: (ለምሳሌ:- የሰረቅሁትን ገንዘብ ለመመለስ ቴፕ ሪከርዴን መሸጥ ካለብኝ)፣ ያንንም ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን አለብኝ:: ገንዘቡን አለመመለስ ማለት በሌላ ሰው ጉዳትና ኃጢአት በመሥራት መጠቀም ማለት በመሆኑ ፍቅርን አያሳይም:: (ማስታወሻ:- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ መስረቅ ማለት ያለ ባለቤቱ ፈቃድ ንብረቱን መዝረፍ ነው:: ዕቃውን ቢጠቀምበትም ባይጠቀምበትም ለውጥ አያመጣም:: ነገሩን ማድረጌን ባለቤቱ አወቀውም አላወቀውም ለውጥ አያመጣም:: ነገሩ ኃጢአት የሚሆነው ሰውየው ሲያውቀው ሳይሆን፣ ገና እንደ ሰረቅን ነው::) ገንዘብ በሆነ የጊዜ ገደብ እከፍላለሁ ብለን ከተበደርንና ባልነው ቀን «አይፈልገውም» ብለን በማሰብ ሳንመልስለት ከቀረን፣ ሰርቀናል ማለት ነው:: ገንዘቡን ከወሰድኩበት ሰው ፈቃድ ውጪ ንብረቱን በመያዜ «ሌባ» ነኝ::

ስለዚህ ይቅርታ እንዲደረግለት የሚጠይቅ ሰው ሁሉ ያደረሰውን ጉዳት ለመቀልበስ መፈለግ አለበት:: ሆኖም፣ ገንዘቡን የወሰድንበት ሰው «ምንም አይደለም:: ገንዘቡን ብትሰርቀኝም፣ ገንዘቡን እንድትመልስልኝ አላስጨንቅህም:: በቃ ተወው» የማለት መብት አለው:: ነገር ግን ያ የሰውየው ምርጫ ነው:: የሰረቀው ሰው ግን ያንን ሊጠብቅና ሊጠይቅ አይገባም::

አንድ ሰው ከቤተ ክርስቲያን መባ ላይ ቢሰርቅስ? ያ ሰው ገንዘቡን እንዲመልስ መጠበቅ አለብን? ሽማግሌዎች ያ ሰው የሰረቀውን ገንዘብ እንዲመልስ ሊያስገድዱት ይገባል? መልሱ «አዎን» ነው:: ሽማግሌዎቹ «በቃ አትክፈል» የማለት ሥልጣን



የላቸውም:: ያንን ማለት የምንችለው ገንዘቡ የእኛ ሲሆን ብቻ ነው:: ነገር ግን መባው ለማን ነው የሚገባው? ገንዘቡ የሽማግሌዎቹ አይደለም:: የቤተ ክርስቲያን ገንዘብም አይደለም:: የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው:: በዚህ ጉዳይ እውነተኛ ንስሐ ካስፈለገ፣ የሚከተሉት ነገሮች መሆን አለባቸው ብዬ አምናለሁ::

ሀ. ይቅርታ እንዲደረግለት የሚፈልገው ሰው የሰረቀውን በሙሉ በተመለከተ ንስሐ መግባት አለበት:: ሰዎች የደረሱበትን ብቻ ንስሐ ከገባ፣ ኃጢአቱን ከልቡ አልተናዘዘም ማለት ነው:: ስለዚህ የሰረቀውን በሙሉ ንስሐ መግባት አለበት::

ለ. ይቅርታ እንዲደረግለት የሚፈልገው ሰውዬ የሰረቀውን ገንዘብ በሙሉ በራሱና በቤተሰቡ ላይ የገንዘብ ችግር ቢያመጣም እንኳን መመለስ አለበት:: እግዚአብሔር ወይም ቤተ ክርስቲያን እርሱ በሠራው ስሕተት ከሚሠቃዩ ይልቅ፣ የኃጢአቱን ሥቃይ ራሱ መቻል አለበት:: በአእምሮው ገንዘቡን እንዴት መመለስ እንዳለበት ዕቅድ ሲያወጣና ሽማግሌዎች የሚጥሉበትን ማንኛውም ቅጣት ለመቀበል መዘጋጀት አለበት:: «ከቤተ ክርስቲያን 1,000 ብር ወስጄ የቤቴን ጣራ በቆርቆሮ አልብሻለሁ:: ምን እንዳደርግ ትፈልጋላችሁ? አሁን 1000 ብር የለኝም:: እኔ እንዲህ አስቤአለሁ፣ ውሳኔው ግን የእናንተ ነው:: ላሜን ልትወስዷት ትችላላችሁ:: ገበያ ላይ 400 ብር ታወጣለች:: በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት፣ አዝመራዬ ሲደርስ፣ በየዓመቱ 3 ኩንታል በቆሎ እሰጣለሁ፣ ያ ደግሞ 600 ብር ያወጣል» ሊል ይችላል::

ሐ. ሰውየውና ቤተሰቡ እንዳይጐዱ ገንዘቡ የሚመለስበትን መንገድ ሽማግሌዎቹ ምሕረትን በተላበሰ አኳኋን ማፈላለግ አለባቸው:: ነገር ግን ሰውየው የሰረቀው ገንዘብ ለሰውየው የበለጠ ምቾትን ካመጣ (ለምሳሌ፣ ሰውየው ተጨማሪ ቤት ወይም መኪና ከገዛ)፣ ሰውየው እነዚያን ሸጦ በፍጥነት ገንዘቡን እንዲመልስ የማድረግ መብት አላቸው:: የሰረቀው ገንዘብ ሕይወቱን ለማቆየት

አስፈላጊ ከሆነ፣ ሊያዝኑለትና ገንዘቡን በረጅም ጊዜ ክፍያ መክፈል እንዲችል አብረውት ሊሠሩ ይገባል። ነገር ግን ገንዘቡ የእነርሱ ባለመሆኑ፣ «በቃ ገንዘቡን ወስደው» ማለት አይችሉም። እንደዚያ ያለ አመለካከት የተቀሩትን የቤተ ክርስቲያን አባላት እምነት የሚያጠፋና በኋላም አብዛኛዎቹ ገንዘብ ሰርቀው የውሸት «ይቅርታ» እንዲጠይቁ የሚፈታተን ነው።

መ. ሰውየው በቤተ ክርስቲያን ሕዝብ ፊት ንስሐ እንዲገባ መጠየቅ አለበት። ገንዘቡን የሰጡት ሁሉም በመሆናቸው፣ ሁሉም ሰው ተጐድቷል። ከዚያ በኋላ ሽማግሌዎቹ ሰውየውን ይቅር እንዳሉት መናገር አለባቸው። መሪ ከሆነ፣ ከኃላፊነቱ እንዲነሣ ማድረጋቸውን መግለጽ ይገባቸዋል። ሰውየው ገንዘቡን እንዴት መመለስ እንዳለበት ያወጡትን ዕቅድ በዝርዝር ማስረዳት አለባቸው። ይህ ደግሞ ለበደለው ሰው ይቅርታ አድርጐ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቅድስና መጠበቅ ያስችላል።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ:- ሀ) በጣም ጥቂት አማኞች ብቻ የሰረቁትን ገንዘብ ለመመለስ የሚፈልጉት ለምን ይመስልሃል? ለ) ይሄ አመለካከት በሰረቀው ሰው ዘንድ እውነተኛ ንስሐ አለመኖሩን እንዴት ያሳያል? ሐ) ሰዎች እስኪደረስባቸው ድረስ የሰረቁትን ነገር የማያምኑት ለምን ይመስልሃል? ይሄ አብዛኛዎቹ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ንጹሕ መሆን እንደማይፈልጉ ምን ያስተምራል? መ) አንድ መሪ ከቤተ ክርስቲያን መባ ላይ ሲሰርቅ አብዛኛ ዎቹ ሽማግሌዎች እንዴት ነው ጉዳዩን የሚይዙት? በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን ዘንድ ይህ ምን ይፈጥራል? ሠ) የሰረቀው ሽማግሌ ከላይ እንደተገለጸው ቢያዝ ምን የተለየ ነገር ይፈጠር ነበር? |

## ሁለተኛ ቀን:- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተለየ ሁኔታ የተጋለጡባቸው ኃጢአቶች (ክፍል 6)

### መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን በሚመሩበት መንገድ ላይ ያሉ ኃጢአቶች (ክፍል 1)

ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚመሩበት መንገድ ላይ



ሊያሸንፋቸው የሚፈልግባቸው የተወሰኑ ኃጢአቶች አሉ። መሪዎች ኢየሱስ እንደ ገለጠው «አገልጋዮች መሪዎች» ከሆንን፣ እነዚህን ኃጢአቶች በሕይወታችን እንዳሉ በማወቅ እናሸንፋቸዋለን። የሚከተሉት ነገሮች መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባላቸው መረዳት ላይ የሚፈታተኗቸው ነገሮች ናቸው።

### 1. ሌሎችን እንደ ባሪያ ከማገልገል ይልቅ የመሪነትን ኃይልና ሥልጣን የመፈለግ ኃጢአት።

«ኃይል በሙስና ይዘፍቃል፣ ፍጹም የሆነ ኃይል ፍጹም የሆነ ሙስና ውስጥ ይዘፍቃል» የሚል የእንግሊዞች አባባል አለ። ይህንን በመንግሥት ላይ እንመለከታለን። የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ወደ ሥልጣን ሲመጡ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚጀምሩት ሕዝቡን ለመርዳት ከመፈለግ ነው። ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ ያላቸውን ኃይል ሲያስቡ ማንነታቸው እየተቀየረ ይሄዳል። እነዚህ ሰዎች አምባ ገነን እየሆኑ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን እያዘዙና ሥልጣናቸውን የሚቃናቀኑትን እያጠፉ ይሄዳሉ።

ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ይከሰታል። ትሑት የቤተ ክርስቲያን አባላት መጀመሪያ ላይ በፈቃዳቸው ደስ እያላቸው ነው የሚጀምሩት፣ ነገር ግን ለመሪነት ከተመረጡ በኋላ ቀስ በቀስ ይቀየራሉ። ምንም እንኳን ቀልደኛ፣ ሰዎችን መርዳት የሚፈልግ የነበሩ ቢሆንም፣ ድንገት አምባ ገነን ሆነው በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን የሚያዝዙ ሰዎች ይሆናሉ።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ:- 2ኛ ሳሙ. 24:1-10ን አንብብ። ሀ) ዳዊት እዚህ ጋ የፈጸመው ኃጢአት ምንድን ነው? ለ) ለምን ይመስልሃል ዳዊት የሌሎችን ምክር ሊሰማ ያልፈለገው? ሐ) ይህ ነገር ሌሎችን ለመስማት ለማይፈልጉና ውሳኔያቸውን ለማስፈጸም ያላቸውን የመሪነት ኃይል በሚጠቀሙ መሪዎች ላይ ስለተጋረጠው አደጋ ምን ያስተምራል? መ) በዘመናችን በርካታ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት በተመሳሳይ ኃጢአት እንደሚወድቁ ግለጽ። |